
# የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ

## ቁጥር 528/2013

መጋቢት 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ



## <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 528/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጉም

   1. በዚህ መመሪያ አዋጅ ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ሲሆን ደንብ ማለት ደግሞ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 392/2009 ማለት ነው፤
   2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተደነገጉት የቃላት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

3. የተፈፃሚነት ወሰን

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 የተፈጻሚነት ወሰን ለዚህ መመሪያም ያገለግላል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

### <u>የንግድ ድርጅት ስም እና የንግድ ስም ስለመመዝገብ፣ ስለማሻሻል ፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ</u>

4. የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ድርጅት ስም ስለመመዝገብ

ማንኛውም የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ድርጅት ስም ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፦

   1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 01 የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ያቀርባል፣
   2. በአዋጁ አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት የንግድ ድርጅት ስሙን ከንግድ ሚኒስቴር ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ በማጣራት ይመዘገባል።

5. የንግድ ማህበር የንግድ ድርጅት ስም ስለመመዝገብ

ማንኛውም የንግድ ማህበር የንግድ ድርጅት ስም ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፦

   1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ቢያንስ ሶስት አማራጭ የንግድ ድርጅት ስሞችን እንዲሞላ ይደረጋል፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives

2. በአዋጁ አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀጽ 2፣3፣4፣5 ድንጋጌ እና በደንቡ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መስፈርት መሰረት የንግድ ማህበር የንግድ ድርጅት ስም ከንግድ ሚኒስቴር ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ በማጣራት ይመዘገባል፤

3. ተጣርቶ የተመዘገበውን የንግድ ድርጅት ስም የማህበሩ የመመስረቻ ፅሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ እንዲጸድቅ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲያገኙ ሰነድን ለማረጋገጥ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለመስጠት በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል በደብዳቤ ይሸኛል፤

4. ተጣርቶ የተሰጠው የንግድ ድርጅት ስም ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ፀድቆ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ወጥቶለት ለመዝጋቢው አካል ቀርቦ የንግድ ምዝገባ ካልተደረገበት እንደተመዘገበ አይቆጠርም፤

5. የተጣራው የንግድ ድርጅት ስም የማይመዘገብ ሆኖ ከተገኘ መዝጋቢው አካል የማይመዘግብበትን ምክንያት ገልፆ ለአመልካቹ ወዲያውኑ በፅሁፍ ያሳውቃል፤

6. የሽርክና ማህበር የአባላቱን ስም በድርጅት ስምነት የሚጠቀም ሲሆን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና የአክሲዮን ማህበር የፈጠራ ስም መጠቀም አለባቸው፤

7. በአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት የሚደረግ የንግድ ድርጅት ስም ምዝገባ የንግድ ምዝገባ በሚያደርግበት ቦታ መመዝገብ አለበት።

6. የንግድ ማህበር የንግድ ድርጅት ስም ስለማሻሻል

ማንኛውም የንግድ ማህበር የንግድ ድርጅት ስም ለማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ | ቅፅ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ቢያንስ ሶስት አማራጭ የንግድ ድርጅት ስሞችን እንዲሞላ ይደረጋል፤

2. የንግድ ማህበር የንግድ ድርጅት ስምን ከንግድ ሚኒስቴር ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ በማጣራት ይመዘገባል፤

3. ለማሻሻያ የተዘጋጀው ያልጸደቀ ቃለ ጉባኤ ለመዝጋቢው አካል እንዲቀርብ ተደርጎ በማጣራት እንዲጸድቅ ሰነድን ለማረጋገጥ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲሻሻል በህግ ስልጣን ለተሰጣቸው አካላት በደብዳቤ ይሸኛል፤

4. ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ ቃለ ጉባኤ እና የድርጅቱ ስም ተሻሽሎ እንዲመዘገብ ከግብር አስከፋዩ መስሪያ ቤት የስምምነት ደብዳቤ ይዞ ሲቀርብ የተሻሻለው የድርጅት ስም ይመዘገባል፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

5. የተሻሻለው የንግድ ድርጅት ስም ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ፀድቆ ለመዝጋቢው ቀርቦ ካልተመዘገበ የቀድሞው የንግድ ድርጅት ስም እንደተሻሻለ አይቆጠርም።

7. የንግድ ስምን ስለመመዝገብ

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ቢያንስ ሶስት አማራጭ የንግድ ስሞችን ሞልቶ እንዲያቀርብ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 5 መስፈርት እና በዚህ መመሪያ መሰረት የንግድ ስሙ ከንግድ ሚኒስቴር ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ ይጣራል፤
3. የተጣራው የንግድ ስም በሌላ ነጋዴ አለመያዙ ከተረጋገጠ በኋላ በአባሪ II ቅጽ 03 የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
4. ተጣርቶ የተሰጠው የንግድ ስም በስህተት ወይም በሌላ ምክንያት ለሌላ ነጋዴ ተሰጥቶ ከተገኘ እና በመስጠቱ ቅሬታ ከቀረበ የንግድ ስሙን ቅድሚያ የወሰደው ነጋዴ ባለመብት እንዲሆን ተደርጎ በኋላ የወሰደው ነጋዴ ሌላ የንግድ ስም እንዲያወጣ ይደረጋል፤
5. በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ በሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች በሚሰጥባቸው የንግድ ስራ መደቦች ላይ የንግድ ስም ምዝገባ ሲጠየቅ አገልግሎቱን የሚያገኙት የንግድ ምዝገባ ባደረጉበት ቦታ ይሆናል፤
6. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም በመታሰቢያነት እንዲመዘገብ ሲጠይቅ በመታሰቢያነት የሚጠቀምበት ስም ባለቤት የቤተሰቡ አባል የነበረ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል።

8. የንግድ ስምን ስለማሻሻል

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም ምዝገባ ለማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ቢያንስ ሶስት አማራጭ የንግድ ስሞችን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 7 መስፈርት መሰረት የንግድ ስሙ ከንግድ ሚኒስቴር ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ውስጥ ይጣራል፤
3. የተጣራው የንግድ ስም በሌላ ነጋዴ አለመያዙ ከተረጋገጠ በኋላ በአባሪ II ቅጽ 03 የተሻሻለበት የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤



ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት

4. ተጣርቶ የተሰጠው የንግድ ስም በስህተት ወይም በሌላ ምክንያት ለሌላ ነጋዴ ተሰጥቶ ከተገኘ እና በመሰጠቱ ቅሬታ ከቀረበ የንግድ ስሙን ቅድሚያ የወሰደው ነጋዴ ባለመብት እንዲሆን ተደርጎ በኋላ የወሰደው ነጋዴ ሌላ የንግድ ስም እንዲያወጣ ይደረጋል፤
5. የተሻሻለው የንግድ ስም በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ በመጠቀም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድረ ገጽ የንግድ ስም እና አድራሻ ይፋ ይደረጋል።

9. ምትክ የንግድ ስም

ማንኛውም ነጋዴ ምትክ የንግድ ስም አገልግሎት ሲጠይቅ፦

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ምትክ የንግድ ስም እንዲሰጠው እንዲጠይቅ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 6 መስፈርት እና በዚህ መመሪያ መሰረት የጠየቀው አገልግሎት በአባሪ II ቅፅ 03 ምትክ የንግድ ስም የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ይደረጋል።

10. የንግድ ስም ስረዛ

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስም ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፦

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 01 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ ስም እንዲሰረዝለት እንዲጠይቅ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 8 መስፈርት መሰረት የተጠየቀውን የንግድ ስም በመሰረዝ እና የተሰረዘው ንግድ ስም የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ ተመላሽ ተደርጎ የስረዛ ማስረጃ ይሰጣል።



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

## ክፍል ሶስት

## የንግድ ምዝገባ ስለመመዝገብ ስለማሻሻል ፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ

11. አገር አቀፍ ተፈፃሚነት ያለው የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በስራ ቋንቋ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

12. የግለሰብ ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ስለመመዝገብ

ማንኛውም ግለሰብ ነጋዴ የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ ምዝገባ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. የጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 9 መሰረት መስፈርቶችን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሰረት የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
3. የግለሰብ ነጋዴ ካፒታል ለንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት አገልግሎት ለማግኘት በሞላው አባሪ I ቅፅ 02 ላይ የመዘገበው የገንዘብ መጠን ካፒታል ነው ተብሎ ይመዘገባል፡፡

13.የንግድ ማህበር የንግድ ምዝገባ ስለመመዝገብ

ማንኛውም የንግድ ማህበር የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ ምዝገባ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. ከአክሲዮን ማህበር ውጭ ያሉ ሌሎች የንግድ ማህበራት በመመስረቻ ፅሁፎቻቸው ላይ የመዘገቡት የገንዘብ መጠን ካፒታል ነው ተብሎ ይመዘገባል፤
3. በአዋጁ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የንግድ ማህበር ስለመቋቋሙ በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድረ ገጽ የድርጅቱ ስም እና አድራሻ ይፋ ይደረጋል፤
4. የጠየቀው አገልግሎት በደንቡ አንቀጽ 10 እና 11 መሰረት መስፈርቶችን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሰረት የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡



ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት

## 14.የንግድ ምዝገባን ስለማሻሻል

ማንኛውም ነጋዴ  የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ  አባሪ I ቅፅ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ  የንግድ ምዝገባ ማሻሻል ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 18 መስፈርት መሰረት የተጠየቀው የማሻሻያ አገልግሎት ሲፈቀድ ቀድሞ የወሰደውን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ በመመለስ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሰረት የተሻሻለ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
3. የንግድ ማህበር የካፒታል ማሻሻያ በሚያደርግበትና የካፒታል ማሻሻያው በጥሬ ገንዘብ በሚሆንበት ጊዜ ገንዘቡ በአባላቱ በእያንዳንዳቸው ስም የተመዘገበበት ሰነድ እና ሰነድን ለማረጋገጥ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፣
4. የንግድ ማህበር የካፒታል ማሻሻያ በሚያደርግበትና የካፒታል ማሻሻያው በዓይነት በሚሆንበት ጊዜ በአባላቱ ሙሉ ድምፅ ስምምነት የተደረገበት ሰነድ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል የፀደቀ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤
5. የንግድ ማህበር የካፒታል ማሻሻያ በሚያደርግበትና የካፒታል ማሻሻያው ከትርፍ ክፍፍል የሚደረግ ከሆነ ማህበሩ ያስመዘገበው ትርፍ ስለመኖሩ በኦዲት ሪፖርት ላይ ተረጋግጦ በአባላቱ ጠቅላላ ስምምነት የተደረገበት ሰነድ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት።

## 15.ምትክ የንግድ ምዝገባ ስለመስጠት

ማንኛውም ነጋዴ  ምትክ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ  አባሪ I ቅፅ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ  ምትክ የንግድ ምዝገባ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 19 መስፈርት መሰረት የተጠየቀው ምትክ የንግድ ምዝገባ አገልግሎት ሲፈቀድ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 01 መሰረት ምትክ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።



Ministry of Trade Archives

16.የንግድ ምዝገባ ስረዛ

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ምዝገባ ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ:-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 02 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ ምዝገባ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር የንግድ ምዝገባ ሲሰረዝ አባላቱ በሰየሙት ሂሳብ አጣሪና በደንቡ አንቀፅ 21 መስፈርት መሟላቱን በማረጋገጥ እና የተሰረዘውን የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ ተመላሽ በማድረግ የንግድ ምዝገባ ስረዛ ደብዳቤ ይሰጣል፤
3. ማንኛውም የንግድ ምዝገባ ስረዛ ሲከናወን መዝጋቢው አካል ስረዛውን ለጠየቀው አካል በደብዳቤ ይገልፃል፤
4. በአዋጁ አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀጽ 7 የንግድ ማህበራት ምዝገባ ስረዛ የሚጸናው የስረዛው ማስታወቂያ በአመልካቹ ወጪ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ከአንድ ወር በኂላ መሆኑ ተረጋግጦ አገልግሎቱ ይሰጣል፤
5. በአዋጁ አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ መሰረት የንግድ ምዝገባ ሳይሰረዝ እንዲራዘም ሲጠየቅና በመዝጋቢው መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ሲወሰን መራዘሙ ለጠያቂውና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል፤
6. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ተፈጻሚነት ሲባል የበላይ ኃላፊ ማለት ከፌዴራል እስከ አካባቢ አስተዳደር ያሉ ንግድን የሚያስተዳድሩ አካላት ናቸው።

17.ስለንግድ ስራ አድራሻ

1. ማንኛውም የንግድ ማህበር የንግድ ስራ አድራሻ ማረጋገጫ በማህበሩ ስም ማቅረብ አለበት፣
2. ለንግድ ስራ አድራሻ የቀረበው የውርስ ሀብት በሚሆንበት ጊዜ በወራሾች ውክልና የተሰጠው ሰው እንደ ውክልናው ዓይነት የውርስ ንብረቱን በአድራሻነት ሊያስመዘግብ የሚችል ሲሆን ውክልና የሌላቸው ወራሾች በተናጠልም ሆነ በጋራ ንብረቱን በንግድ ስራ አድራሻነት ሊያስመዘግቡ አይችሉም ሆኖም ግን በወኪላቸው የተረጋገጠ ይሁንታ በማቅረብ ሊያስመዘግቡ ይችላሉ፣
3. ማንኛውም ነጋዴ ከሃይማኖት ተቋማት፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የንግድ ቤት ሲከራይ ውሉ በህግ ሰነዶችን ለማረጋገጥ ስልጣን በተሰጠው



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

አካል እንዲረጋገጥ አይገደድም።ሆኖም በተቋማቱ ማህተም የተረጋገጠ የኪራይ ውል መቅረብ አለበት፣

4. ማንኛውም የህንጻ አከራይነት የንግድ ስራ ፈቃድ ያለው ግለሰብ ወይም ማህበር የንግድ ቤት ሲያከራይ ውሉ በህግ ሰነዶችን ለማረጋገጥ ስልጣን በተሰጠው አካል እንዲረጋገጥ አይገደድም፤ ሆኖም በተቋሙ ማህተም የተረጋገጠ የኪራይ ውል እና የግለሰቡ ወይም የማህበሩ የህንጻ አከራይነት የፀና ንግድ ስራ ፈቃድ ኮፒ ተያይዞ መቅረብ አለበት፤
5. የንግድ ስራ አድራሻ የባለቤትነት ይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው በባል ወይም በሚስት ስም የሆነ ግለሰብ ነጋዴ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በማቅረብ ከሁለቱ በአንዳቸው ስም በንግድ ስራ አድራሻነት መጠቀም ይችላሉ፣ ሆኖም ግን በባለይዞታው በማናቸውም ግዜ ተቃውሞ በፅሁፍ ከቀረበ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አድራሻው ሊሰረዝ ይችላል፤
6. ለጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ስራዎች የመስሪያ ቦታ ሲሰጥ ይህንኑ የሚገልፅ ሰነድ ከሚመለከተው አካል መቅረብ አለበት፤
7. የግለሰብ ነጋዴ ሆኖ የስራ ባህርይው የንግድ ስራ አድራሻ የማይጠይቅ እንደ አናጺ፣ ግምበኛ፣ቀለም ቀቢ እና የመሳሰሉት በሚሆንበት ጊዜ የመኖሪያ አድራሻው የንግድ ስራ አድራሻ ነው ተብሎ ይወሰዳል፤
8. በትራንስፖርት ስራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች የአድራሻ ማረጋገጫ በቀበሌ መታወቂያው ላይ የተመዘገበው አድራሻ ይሆናል፤

18.በማዕድን ዘርፍ የተሰማራ የውጭ ሀገር ነጋዴ የንግድ ምዝገባን በተመለከተ በዓለም ዓቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆነው ለሚገቡ የውጭ ሀገር ድርጅቶች የተቀመጠው መስፈርት (ከውል ስምምነት ሰነድ በስተቀር) የሚያገለግል ሆኖ በተጨማሪ ማዕድንን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የይመዝገብልኝ የድጋፍ ደብዳቤ ማምጣት አለበት።



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

## ክፍል አራት

## የንግድ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት ፣ስለማደስ ፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ

19. የንግድ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስራ ፈቃድ ለማግኘት አገልግሎት ሲጠይቅ፦

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ ስራ ፈቃድ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 23፣24፣25 እና 26 ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የተጠየቀው የንግድ ስራ ፈቃድ አገልግሎት ሲፈቀድ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 02 መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
3. በዓለም ዓቀፍ ጨረታ አሸናፊ ሆኖ የሚገባ ነጋዴ በጨረታ አሸናፊ ከሆነበት የንግድ ስራ በተጨማሪ ሌላ ጨረታ ያሸነፈ ከሆነ ላሸነፈበት ጨረታ ተጨማሪ የንግድ ስራ ፈቃድ የማውጣት ግዴታ አለበት፤
4. በደንቡ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ግለሰብ ነጋዴ ቀደም ሲል የንግድ ስራ ፈቃድ በማናቸውም ቦታ ያወጣ ከሆነ ተጨማሪ የንግድ ስራ ፈቃድ በውክልና ማውጣት ይችላል።

20. የንግድ ስራ ፈቃድ ስለማደስ

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስራ ፈቃድ ለማደስ አገልግሎት ሲጠይቅ፦

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ ስራ ፈቃድ ዕድሳት ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 30 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 02 መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ ዕድሳት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
3. ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በንግድ ህጉ መሠረት የአባላቱ ቁጥር ሃያ እና ከሃያ በታች በሚሆንበት ጊዜ በውስጥ ኦዲተር የተመረመረ የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ከሃያ በላይ አባላት ሲኖረው በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የኦዲት ሪፖርት ያቀርባል፤
4. ኃላፊነቱ ያልተወሰነ የንግድ ማኅበር በዕድሣት ወቅት የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርብ አይገደድም፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

5. በአዋጁ አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር ካስመዘገበው ካፒታል ሶስት አራተኛውን ወይም ከዚያ በላይ ኪሳራ ያስመዘገበ በሚሆንበት ጊዜ የገባው ተጨማሪ ገንዘብ አባላቱ ባዋጡት መነሻ ካፒታል ላይ ተጨምሮ ይመዘገባል፤
6. የአክሲዮን ማህበር ለንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፣
7. ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር በእድሳት ወቅት የሚያቀርበው የኦዲት ሪፖርት ሁለት የበጀት ዓመት ያላለፈው መሆን አለበት፤
8. አዲስ የሚቋቋም ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር እስከ ሁለት የበጀት አመት የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርብ አይገደድም፤
9. የንግድ ስራ ፈቃዱን ባለማሳደሱ በአዋጁ የተሰረዘበት የግለሰብ ነጋዴ ያንኑ ፈቃድ መልሶ በውክልና ማውጣት ይችላል፤
10. ኃላፊነቱ የተወሰነ የንግድ ማህበር የንግድ ስራ ፈቃድ ለማሳደስ የንግድ ማህበሩ ስራ አስኪያጅ ወይም ህጋዊ ውክልና በተሰጠው ሰው መታደስ ይችላል፤
11. የመረጃ መረብ ባለበት ቦታ ሁሉ የቀረበው የግብር ክሊራንስ ትክክለኛ ስለመሆኑ ግብር ለመሰብሰብ በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል የመረጃ መረብ መረጋገጥ አለበት፤
12. ግብርን ለመሰብሰብ ስልጣን ከተሰጠው አካል ጋር የመረጃ መረብ ግንኙነት በሌለበት ቦታ የቀረበው የግብር ክሊራንስ ግብር ለመሰብሰብ በህግ ስልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠው መረጃ ትክክለኛ ነው ተብሎ ይወሰዳል፤
13. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 11 እና 12 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረበው የግብር ክሊራንስ ትክክለኛ ስለመሆኑ አመቺ በሆነው መንገድ ሁሉ መዝጋቢው አካል ማረጋገጥ ይችላል፤
14. ቀደም ሲል በየትኛውም የስራ መደብ የንግድ ስራ ፈቃድ አውጥቶ ሲሰራ ቆይቶ በማንኛውም ምክንያት የንግድ ስራ ፈቃዱ የተሰረዘበት ወይም በቅጣት ላይ ያለ ነጋዴ አዲስ የንግድ ስራ ፈቃድ ሲያወጣ ቀድሞ ሲሰራበት ለነበረው የንግድ ስራ ፈቃድ የግብር ክሊራንስ ማቅረብ አለበት፤
15. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስራ ፈቃዱ በአዋጁ መሰረት ካልተሰረዘ በእድሳት ወቅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም ደብዳቤ እንዲያቀርብ አይገደድም፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

16. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማያስፈልጋቸውን የንግድ ስራ ፈቃድ መደቦችን በተመለከተ በቀጣይ ክለሳ በሚደረገው የኢትዮጵያ ንግድ ስራ ፈቃድ መስጫ መመሪያ ላይ እንዲወጣ ይደረጋል።

21. የንግድ ስራ ፈቃድ ስለማሻሻል

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስራ ፈቃድ ለማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ፦

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ ስራ ፈቃድ የማሻሻል ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 32 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 02 መሰረት የተሻሻለ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

22. ስለ ምትክ የንግድ ስራ ፈቃድ

ማንኛውም ነጋዴ ምትክ የንግድ ስራ ፈቃድ አገልግሎት ሲጠይቅ፦

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ምትክ የንግድ ስራ ፈቃድ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. የደንቡ አንቀፅ 33 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ተረጋግጦ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 02 መሰረት ምትክ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

23. የንግድ ስራ ፈቃድ ስረዛ

ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ስራ ፈቃድ ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፦

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 03 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ ስራ ፈቃድ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 35 መሰረት መስፈርቱ መሟላቱ ሲረጋገጥ የንግድ ስራ ፈቃዱ ዋና ቅጂ ተመላሽ ተደርጎ የተጠየቀው የንግድ ስራ ፈቃድ ስረዛ ማስረጃ ደብዳቤ ይሰጣል፤
3. ማንኛውም የንግድ ስራ ፈቃድ ሲሰረዝ ስረዛውን ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል።

24. የዘርፍ ማህበራት፣ የውጭ ሀገር ንግድ ምክር ቤቶች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ምዝገባ ፣ የሆልዲንግ ኩባንያ እና የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ

ማንኛውም አመልካች የዘርፍ ማህበር፣ የውጭ ሀገር ንግድ ምክር ቤት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምዝገባ፣ የሆልዲንግ ኩባንያ ወይም የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ፦



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 04 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 16 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 06 መሰረት የዘርፍ ማህበራት ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
3. በደንቡ አንቀፅ 17 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 07 መሰረት የውጭ ሀገር ንግድ ምክር ቤቶች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
4. በደንቡ አንቀፅ 37 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 08 መሰረት የሆልዲንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
5. በደንቡ አንቀፅ 48 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 09 መሰረት የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

25.የሆልዲንግ እና የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ ዕድሳት

ማንኛውም አመልካች የሆልዲንግ ወይም የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ ዕድሳት አገልግሎት ሲጠይቅ፦

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 04 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የልዩ ምዝገባ ዕድሳት ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤

የተጠየቀው አገልግሎት

ሀ. በደንቡ አንቀጽ 38 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 08 መሰረት የሆልዲንግ ልዩ ምዝገባ ዕድሳት ይደረጋል፤

ለ. በደንቡ አንቀጽ 49 ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 09 መሰረት የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዕድሳት ይደረጋል፤

2. በፍራንቻይዝ ውሉ መሰረት ፍራንቻይዘሩ ከሚያገኘው ገቢ ተገቢውን ግብር መክፈሉን ከግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ማስረጃ ያቀርባል።



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

26. የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ ምዝገባን ስለማሻሻል

ማንኛውም አመልካች የሆልዲንግ ኩባንያ ልዩ ምዝገባ ምስክር ወረቀት የማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 04 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የልዩ ምዝገባ ማሻሻል ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 40 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ ቀድሞ የወሰደውን የልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት በመመለስ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 08 መሰረት የተሻሻለ የሆልዲንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

27. የሆልዲንግ ኩባንያ እና የፍራንቻይዚንግ ምትክ የልዩ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ማንኛውም አመልካች የሆልዲንግ ኩባንያ ወይም የፍራንቻይዚንግ ምትክ የልዩ ምዝገባ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 04 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ምትክ የልዩ ምዝገባ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 39 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 08 መሰረት ምትክ የሆልዲንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
3. በደንቡ አንቀፅ 50 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 09 መሰረት ምትክ የፍራንቻይዚንግ ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

28. የሆልዲንግ ኩባንያ እና የፍራንቻይዚንግ የልዩ ምዝገባ ስረዛ

ማንኛውም አመልካች የሆልዲንግ ኩባንያ ወይም የፍራንቻይዚንግ የልዩ ምዝገባ ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 04 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የልዩ ምዝገባ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. የልዩ ምዝገባ አገልግሎት የግብር መዝጊያ ክሊራንስ ማቅረብ አለበት፤
3. በደንቡ አንቀጽ 41 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ መሰረት የሆልዲንግ ኩባንያ የልዩ ምዝገባ ስረዛ ደብዳቤ ይሰጣል፤
4. በደንቡ አንቀጽ 51 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ መሰረት የልዩ ምዝገባ ስረዛ ደብዳቤ ይሰጣል፤



ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archive መዝገብ ቤት

5. ማንኛውም የሆልዲንግ ኩባንያ ወይም የፍራንቻይዚንግ የልዩ ምዝገባ ሲሰረዝ ስረዛውን ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል፡፡

29. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ማንኛውም የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ለማግኘት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 06 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 27 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 05 መሰረት የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

30. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለማደስ

ማንኛውም የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት የማደስ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 06 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት የማደስ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 31 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 05 መሰረት የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ዕድሳት ይሰጣል፤
3. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ባለማሳደሱ በአዋጁ የተሰረዘበት የንግድ እንደራሴ ያንኑ ፈቃድ መልሶ በውክልና ማውጣት ይችላል፡፡

31. የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስለማሻሻል

ማንኛውም የንግድ እንደራሴ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት የማሻሻል አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 06 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ማሻሻል ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. የተጠየቀው የማሻሻያ አገልግሎት ሲፈቀድ ቀድሞ የወሰደውን የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት በመመለስ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 05 መሰረት የተሻሻለ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

32. ስለ ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት

ማንኛውም የንግድ እንደራሴ ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-



ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 06 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 34 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 05 መሰረት ምትክ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

33. የእንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስረዛ

ማንኛውም የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 06 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 36 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 05 መሰረት የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ ተመላሽ ተደርጎ ስረዛ ይደረጋል፤
3. ማንኛውም የንግድ እንደራሴ ልዩ የምስክር ወረቀት ሲሰረዝ ስረዛውን ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል፡፡

34. የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ስራ እንዲሰራ የተፈቀደለት ነጋዴ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 07 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 42 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 10 መሰረት የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

35. የጠረፍ ንግድ ምዝገባ ስረዛ

ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 07 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የጠረፍ ንግድ ምዝገባ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 43 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ የተጠየቀው የጠረፍ ንግድ ምዝገባ ስረዛ ይደረጋል፤
3. ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ምዝገባ ሲሰረዝ ስረዛውን ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል፡፡



ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት

36. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት

ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ እንዲያወጣ የተፈቀደለት ነጋዴ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 08 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 44 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 11 መሰረት የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

37. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ስለማደስ

ማንኛውም ነጋዴ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ እድሳት አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 08 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ የማደስ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 45 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 11 መሰረት የጠረፍ ንግድ ልዩ ንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ዕድሳት አገልግሎት ይሰጣል፤
3. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ባለማሳደሱ በአዋጁ የተሰረዘበት ነጋዴ ያንኑ ፈቃድ መልሶ በውክልና ማውጣት ይችላል፡፡

38. ስለ ምትክ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ

ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ምትክ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 08 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ ምትክ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤
2. በደንቡ አንቀፅ 46 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ አባሪ II ቅጽ 11 መሰረት ምትክ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

39. የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ስረዛ

ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ስረዛ አገልግሎት ሲጠይቅ፡-

1. በዚህ መመሪያ አባሪ I ቅፅ 08 በተዘጋጀው የማመልከቻ ቅፅ ላይ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ስረዛ ጥያቄውን እንዲሞላ ይደረጋል፤



Ministry of Trade Archives

2. በደንቡ አንቀፅ 47 መሰረት መስፈርት መሟላቱ ሲረጋገጥ የተጠየቀው የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ስረዛ ይደረጋል፤
3. ማንኛውም የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ስራ ፈቃድ ሲሰረዝ ስረዛው ለጠየቀው እና ለሚመለከተው አካል በደብዳቤ ይገለፃል።

## ክፍል አምስት

## ስለ ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን

40. ኢንስፔክሽን ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተግባራት

1. የንግድ ስራ ፈቃድ ሳይኖራቸውና በህግ እና በአስተዳደራዊ እርምጃ የንግድ ስራ ፈቃዳቸው ተሰርዞ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ የንግድ ድርጅቶችን በመመርመር ያረጋግጣል፤
2. የንግድ ስራ ፈቃድ ኖሮአቸው ከተፈቀደላቸው ዓላማ ውጭ የሚሰሩትን የንግድ ድርጅቶችን በመመርመር ያረጋግጣል፤
3. በንግድ ስራ ፈቃድ ዕድሳት ጊዜ ውስጥ የንግድ ስራ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ የሚሰሩ የንግድ ድርጅቶችን በመመርመር ያረጋግጣል፤
4. ማንኛውም ነጋዴ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስፈልጉትን መስፈርት ተሟልቶ አገልግሎት የተሰጠ መሆኑን ከንግድ ደርጅቶች ፋይል ወይም ሰነድ በማጣራት እና ማረጋገጥ አለበት፤
5. ማንኛውም የንግድ ስራ ፈቃድ የተሰጠው ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 26 መሰረት የተጣለበትን ግዴታዎች አሟልቶ መሰራቱን በመመርመር ያረጋግጣል፤
6. ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ ህጎች መሰረት ያገኘውን መብት ለሌላ ሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠትን በመመርመር ያረጋግጣል፤
7. የሚወሰዱ አሰተዳደራዊ እርምጃዎችን ተግባራዊነትን በመመርመር ያረጋግጣል፤

41. በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በአስተዳደራዊ እርምጃ የንግድ ስራ ፈቃዳቸው ተሰርዞ ወይም የንግድ ስራ ፈቃድ ሳይኖራቸው በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩትን ፤ ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዛግብ ቤት

1. በአዋጁ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በንግድ መደብር ውስጥ የንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ነጋዴ እየሰራ ባለው የስራ ዘርፍ በዘመኑ የተሰጠ ወይም የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ያለው መሆኑን በመመርመር ያረጋግጣል፤
2. በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) ፣ (ሐ) እና አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ1 (ለ)፣(ሐ) መሰረት በታገደ ወይም በተሰረዘ የንግድ ስራ ፈቃድ እየተሰራ አለመሆኑን በመመርመር ያረጋግጣል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ ሳይኖራቸው ወይም በታገደ እና በተሰረዘ የንግድ ስራ ፈቃድ የሚሰሩትን ለኢንስፔክሽን ስራ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅፅ 01 ቼክሊስት መሰረት አስፈላጊውን መረጃ በመሙላትና ተጨማሪ መረጃ በመያዝ አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ኢንስፔክተሩ ለቅርብ ሀላፊ ያቀርባል፤
4. በሚቀርበው የኢንስፔክሽን ውጤት መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ ሳይኖራቸው ወይም በተሰረዘ የንግድ ስራ ፈቃድ የሚሰሩ ነጋዴዎች በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

42. የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው ሆነው ከተፈቀደላቸው የስራ መደብ ውጭ የሚሰሩትን ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ

1. ማንኛውም ነጋዴ የፀና የንግድ ስራ ፈቃድ ያለው ሆኖ ነገር ግን እየሰራ ያለው ከተፈቀደለት የንግድ ስራ መደብ ውጭ መሆኑን በኢንስፔክሽን ስራ በማጣራትና በማረጋገጥ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅፅ 01 ቼክሊስት መሰረት አስፈላጊውን መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ኢንስፔክተሩ ለቅርብ ኃላፊ ያቀርባል፤
2. በሚቀርበው የኢንስፔክሽን ውጤት መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ ያለው ሆኖ ከተፈቀደለት የንግድ ስራ መደብ ውጭ የሚሰራ ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

43. የንግድ ስራ ፈቃድ ሳያሳድስ የሚሰራ ነጋዴ ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ፣

1. ማንኛውም ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በበጀት ዓመቱ ባልታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ እየሰራ መሆኑን በማጣራትና በማረጋገጥ ለኢንስፔክሽን ስራ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅፅ 01 ቼክሊስት መሰረት አስፈላጊውን



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዛግብት

መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ኢንስፔክተሩ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለቅርብ ሀላፊ ያቀርባል፤

2. በሚቀርበው የኢንስፔክሽን ውጤት መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ ሳያሳድስ የሚሰራ ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

44. የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ለማግኘት የተቀመጠውን መስፈርት ተሟልቶ አገልግሎት የተሰጠ መሆኑን ከነጋዴው ፋይል ወይም ሰነድ ስለማጣራት እና ስለማረጋገጥ

1. ማንኛውም ነጋዴ በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ለማግኘት የተቀመጡ መስፈርቶች ተሟልተው አገልግሎት ስለመሰጠቱ በውስጥ ኢንስፔክሽን ስራ በማጣራትና በማረጋገጥ መስፈርት ሳያሟላ ወይም ሀሰተኛ መረጃ አቅርቦ አገልግሎት ባገኘ ነጋዴ ላይ አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ መረጃ በማደራጀት የውሳኔ ሃሳብ ለቅርብ ኃላፊው ይቀርባል፤
2. በውስጥ ኢንስፔክሽን ውጤት መሰረት መስፈርት ሳያሟላ ወይም ሀሰተኛ መረጃ አቅርቦ አገልግሎት ያገኘ ነጋዴ በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1/መ እና አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

45. በአዋጁ አንቀጽ 26 መሰረት ነጋዴው ግዴታዎችን ስለማሟላቱ ማጣራትና ማረጋገጥ

1. ነጋዴው ባስመዘገበው አድራሻ የሚገኝ ስለመሆኑ የማጣራትና የማረጋገጥ፤
2. ነጋዴው የአድራሻ ለውጥ አድርጎ ያስመዘገበ ስለመሆኑ መመርመርና ማረጋገጥ አለበት፤
3. ጅምላ ከጅምላ ወይም ችርቻሮ ከችርቻሮ በተመሳሳይ ደረጃ የሚደረግ ግብይት እየተፈፀመ ያለመሆኑን መመርመርና ማረጋገጥ አለበት፤
4. ነጋዴው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሲጠይቅ ትክክለኛ መረጃዎችን በማቅረብ ያስመዘገበ ስለመሆኑ መመርመርና ማረጋገጥ አለበት፤
5. የንግድ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዋጋ ዝርዝር በግልጽ በሚታይ ቦታ መቀመጡን ወይም በንግድ ዕቃዎች ላይ መለጠፉን መመርመርና ማረጋገጥ አለበት፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

6.በተጠቃሚው ሕዝብ ጤንነትና ደህንነት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የተለያዩ የንግድ ዕቃዎች በአንድ ስፍራ እያካሄደ መሆኑን በውጭ ኢንስፔክሽን ስራ መመርመርና ማረጋገጥ አለበት፤

7.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 6 መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ ነጋዴ በመለየት ለኢንስፔክሽን ስራ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅፅ 01 ቼክሊስት መሰረት መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሃሳብ ይቀርባል፤

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በውጭ መሰረት የተጣለበትን ግዴታዎች ያልተወጣ ነጋዴ ጉድለቱን እንዲያስተካክል የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ይሰጣል፤

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት ነጋዴው ጉድለቱን ያላስተካከለ ከሆነ መረጃ ተደራጅቶ ተጨማሪ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል።

46. በአዋጁ መሰረት ነጋዴው የንግድ ስራ ፈቃዱን ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠቱን ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ

1. በውጭ ኢንስፔክሽን ውጤት እና በሚቀርብ ጥቆማ መሰረት የንግድ ስራ ፈቃድ ለሌላ ሶስተኛ ወገን እንዲነግድበት የሰጠ ወይም ያከራየ እንዲሁም በህግ እንዲነግዱ ላልተፈቀደላቸው የውጭ አገር ዜጎች የንግድ ስራ ፈቃድ አሳልፎ የሰጠ ወይም ያከራየ በማጣራት እና በማረጋገጥ ለኢንስፔክሽን ስራ በተዘጋጀው አባሪ IV ቅፅ 01 ቼክሊስት መሰረት መረጃ በመሙላት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሃሳብ ለቅርብ ኃላፊ ይቀርባል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የንግድ ስራ ፈቃዱን አሳልፎ ለሶስተኛ ወገን ሰጥቶ ከተገኘ በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) እና አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ እና አስፈላጊ መረጃዎችን በማደራጀት ለህግ እንዲቀርብ ይደረጋል።

47. የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ተግባራዊነት ስለማጣራትና ስለማረጋገጥ

የአዋጁ፣ የደንቡና እና የዚህ መመሪያ ደንጋጌዎች በመጣሳቸው የሚወሰደውን አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ በትክክል ተግባራዊ መሆኑን በውጭ ኢንስፔክሽን የማጣራት እና የማረጋገጥ ስራ በማከናወን ተግባራዊ ባላደረጉት የንግድ ድርጅቶች ላይ



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

በተላለፈው ውሳኔ መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ መረጃዎችን በማደራጀት ለህግ እንዲቀርቡ ይደረጋል።

48. የውጭ ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክተር ሊፈጽመው የሚገባ ተግባርና ግዴታዎች

1. ኢንስፔክተር መሆኑን የሚገልፅ ልዩ መታወቂያ ወረቀት ቁጥጥር ለሚደረግበት የንግድ ድርጅት የማሳየት አለበት፤
2. የቁጥጥር ስራውን በተመለከተ ቁጥጥር ለሚደረግበት የንግድ ድርጅት ስለሚደረገው ቁጥጥር ማስረዳት አለበት፤
3. በቁጥጥር ስራ የታየውን ጉድለት ለንግድ ድርጅቱ ባለቤት ወይም ተወካይ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፤
4. ተቆጣጣሪው ለቁጥጥር ተግባር ሲወጣ የቁጥጥር ተግባራትን ለማስተባበር የተመደበው አግባብ ያለው ኃላፊ ጋር ስለሚቆጣጠረው የንግድ ድርጅት እና ስለሚደረገው ቁጥጥር ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ IV በሆነው ቅጽ 02 መሠረት ስምምነት ማድረግ አለበት፤
5. ተቆጣጣሪው የቁጥጥር ተግባሩን የሚያከናውነው በመንግስት የስራ ሰዓት ብቻ ሆኖ ነገር ግን አስፈለጊ ሆኖ ሲገኝ ከመንግስት የስራ ሰዓት ውጪ ቁጥጥር ለማድረግ የንግድ ድርጅቱን ስም የሚግለፅ ልዩ ደብዳቤ ከመስሪያ ቤቱ የመያዝና ማሳየት አለበት፤
6. ተቆጣጣሪው ባደረገው የቁጥጥር ተግባር ያገኘውን ውጤት በዚህ መመሪያ አባሪ IV ቅጽ 01 በመሙላት ቁጥጥር ከተደረገበት የንግድ ድርጅት ጋር በመፈራረም ለቅርብ ኃላፊው ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ማቅረብ አለበት፣
7. በቀረበው የኢንስፔክሽን ውጤት እና አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የተወሰነውን አስተዳደራዊ እርምጃ ማስፈፀም አለበት፤
8. አንድ የንግድ ድርጅት በተወሰደ የእርምት እርምጃ መሰረት የታየበትን ጉድለት ስለማስተካከሉ የውጭ ኢንስፔክተሩ በድጋሚ በንግድ ድርጅቱ በመገኘት ያረጋግጣል፤
9. ኢንስፔክተሩ የንግድ ድርጅት እሽጋ የሚያከናውን ከሆነ ነጋዴው ወይም ንግዱን ለማከናወን የተወከለ ሰው እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጸጥታ አካል ባለበት አስተዳደራዊ እርምጃውን የመፈጸም ግዴታዎች አለበት።

49. ቁጥጥር የሚደረግበት ነጋዴ መብትና ግዴታ

1. ነጋዴው የተቆጣጣሪውን ማንነት የሚገልፅ ልዩ የመታወቂያ ወረቀት የመጠየቅና የማየት መብቱ የተጠበቀ ነው፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

2. የቁጥጥር ስራውን በተመለከተ ማንኛውንም መረጃ የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው፣
3. ነጋዴው ለኢንስፔክሽን ስራ ሲጠየቅ የንግድ ስራ ቦታውን በስራ ሰዓት የመክፈት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከስራ ሰዓት ውጭ ክፍት የማድረግ ግዴታ አለበት፤
4. የንግድ ስራ ፈቃድ እና ሌሎች ከንግድ ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ግዴታ የገባባቸውን መረጃዎች ይዞ የመገኘት ግዴታ አለበት።

50. የአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ ስርዓት

1. ኢንስፔክተሩ በኢንስፔክሽን የተገኙ ጉድለቶችን በመረጃና በሪፖርት በማጠናቀር ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለቅርብ ሀላፊ ያቀርባል፤
2. የቅርብ ኃላፊው በቀረበው የኢንስፔክሽን ውጤት እና የውሳኔ ሀሳብ ላይ በመመስረት እና በመረጃ በማስደገፍ ከአዋጁና ደንቡ ጋር አገናዝቦ የራሱን የውሳኔ ሀሰብ ለስራ ክፍል ኃላፊው ያቀርባል፤
3. የስራ ክፍል ኃላፊው የቀረበለትን የኢንስፔክሽን ውጤት እና የውሳኔ ሃሳብ ከተያዘው መረጃ እንዲሁም በአዋጁ፣ በደንቡ እና በዚህ መመሪያ በተዘረዘረው የአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ ስርዓት መሰረት ውሳኔ በመስጠት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤ ሆኖም ከስራ ክፍሉ ኃላፊ መወሰን የማይቻሉት ጉዳዮች ሲገጥሙት የስራ ሂደት ኃላፊውን በማማከር ውሳኔ ይሰጣል ፣ውሳኔው ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

51. በነባር ንግድ ማህበር ውስጥ አባል ለመሆን የሚገባ የውጭ አገር ዜጋ ወይም የውጭ አገር የንግድ ማህበር

በነባር ንግድ ማህበር ውስጥ አባል ለመሆን የሚገባ የውጭ አገር ዜጋ ወይም የውጭ አገር የንግድ ማህበር የሚከተሉትን መረጃዎች ማሟላት አለበት።

1. የተሰማራበት የስራ መስክ ለውጭ አገር ባለሀብት የተፈቀደ መሆኑ ያረጋግጣል፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

2. የአባልነት ጥያቄው በንግድ ውድድርና ሸማቶች ጥበቃ ባለሥልጣን የሚታይ ከሆነ ከዚህ አካል የተሰጠ የፈቃድ ማረጋገጫ መቅረብ አለበት፤

3. በንግድ ማህበር ውስጥ አባል ለመሆን የሚገባ የውጭ አገር ዜጋ ወይም የውጭ አገር የንግድ ማህበር ወደ ነባሩ የንግድ ማህበር እንዲገባ መስማማቱን የሚገልጽ የነባር ንግድ ማህበሩ ያልፀደቀ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤

4. ኢንቨስትመንትን በሚያስተዳድሩ ህጎች ለውጭ አገር ባለሀብት የተደነገገው አነስተኛ ካፒታል ወደ ሀገር ውስጥ ባንክ ያስገባበት ማረጋገጫ መቅረብ አለበት፤

5. ወደ ነባሩ የንግድ ማህበር አክሲዮን ገዝቶ የሚገባው የውጭ አገር የንግድ ማህበር ስምምነትን የሚያሳይ ማስረጃ መቅረብ አለበት፤

6. የነባሩ ንግድ ማህበር የጸና የንግድ ስራ ፈቃድ መቅረብ አለበት፤

7. መዝጋቢው አካል መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ቃለ ጉባኤው እንዲጸድቅ የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፤

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ቃለ ጉባኤው ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ጸድቆ ለመዝጋቢው አካል መቅረብ አለበት።

52. የንግድ መደብርን/ድርጅትን ስለማስተላለፍ የሚጠየቁ መስፈርቶች

1. የንግድ መደብሩ/ድርጅቱ ሲተላለፍ ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ ውል መቅረብ አለበት፤

2. የነባሩ ንግድ ስራ ፈቃድ የግብር መዝጊያ ክሊራንስ መቅረብ አለበት፣

3. የቀድሞ ባለቤት በስሙ የነበረውን የንግድ ስራ ፈቃድ ተመላሽ ማድረግ አለበት፣

4. የንግድ መደብሩ/ድርጅቱ የተላለፈ መሆኑ በአገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ከተነገረበት ከአንድ ወር በኋላ ማስረጃ በማቅረብ የተላለፈለት ግለሰብ በስሙ የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፈቃድ ማውጣት ይችላል፣

5. የሚተላለፈው የንግድ መደብር የንግድ ማህበር በሆነ ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተገለፀው በተጨማሪ ማህበሩ ለማስተላለፍ አባላቱ በሙሉ ድምፅ የተስማሙበት ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

6.የሚተላለፈው የንግድ መደብር ለንግድ ማህበር ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 ከተገለፀው በተጨማሪ የሚተላለፍለት የንግድ ማህበር የመመስረቻ ፅሁፍ፣ የመተዳደሪያ ደንብ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የሚተላለፍለት የንግድ ማህበር አባላት በሙሉ ድምፅ የተደረገ ስምምነት የፀደቀ ቃለ ጉባዔ መቅረብ አለበት፣

7. የሚተላለፈው የንግድ መደብር ለውጭ ሀገር ዜጋ ከሆነ ወይም የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው አባል የሚገኝበት የንግድ ማህበር ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማቅረብ አለበት።

53. ስለንግድ ኩባንያዎች ውህደት

1. የንግድ ኩባንያዎች በሚዋሃዱበት ጊዜ ውህደቱ በንግድ ውድድርና ሸማቶች ጥበቃ ባለሥልጣን የሚታይ ከሆነ ከዚህ አካል የተሰጠ የውህደት ፈቃድ ማረጋገጫ እና በሚዋሃዱት ኩባንያዎች ሙሉ አባላት የተፈረመ እና ሰነዶችን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤
2. ውህደቱ በንግድ ውድድርና ሸማቶች ጥበቃ ባለሥልጣን የማይታይ ከሆነ በሚዋሀዱት የንግድ ኩባንያዎች ሙሉ አባላት ድምጽ የተስማሙበት እና ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤
3. የሚዋሀዱ ማንኛውም የንግድ ኩባንያዎች በተናጠል የመዝጊያ የግብር ክሊራንስ ማቅረብ አለባቸው፣ሆኖም ሲዋሃዱ ዕዳን ለማጠቃለል የተስማሙ ከሆነ የስምምነቱ ማረጋገጫ ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን የተረጋገጠ ማስረጃ መቅረብ አለበት፤
4. የሚዋሀዱ ማንኛውም የንግድ ኩባንያዎች ውህደቱ የሚጠቀምበት የድርጅትና የንግድ ስሞችን በመለየት ማቅረብ አለባቸው፤
5. የሚዋሀዱ ማንኛውም የንግድ ኩባንያዎች ከሚዋሀዱት ኩባንያዎች የድርጅት ስም እና የንግድ ስም ውጪ ሌላ አዲስ የድርጅት እና/ወይም የንግድ ስም የሚጠቀሙ ከሆነ የነበራቸው የድርጅት እና የንግድ ስሞች እንዲሰረዙ ይደረጋሉ፤ አዲሱን ስም በቃለ ጉባዔ በማሻሻል ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል እንዲጸድቅ መደረግ አለበት፤
6. የንግድ ኩባንያዎች ከሚዋሃዱት የንግድ ኩባንያዎች የአንዱን የድርጅትና የንግድ ስም የሚጠቀሙ ከሆነ የተቀሩት የድርጅትና የንግድ ስሞች እንዲሰረዙ ይደረጋል።



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

54. ስለንግድ ኩባንያዎች መከፈል

1. የሚከፈል የንግድ ኩባንያ ከመከፈሉ በፊት የገቢ ክሊራንስ ማቅረብና የሂሳብ መዝገቡን ማዘጋት አለበት፤
2. የሚከፈለው የንግድ ድርጅት የተከፈለው አካል ከሌላ የንግድ ኩባንያ ጋር የሚዋሃድ ከሆነ በሚዋሃደው የንግድ ኩባንያ የድርጅት ስምና የንግድ ስም ይጠቃለላል፤
3. የሚከፈለው የንግድ ኩባንያ የተከፋፈሉ አካሎች ራሳቸውን ችለው የሚመሰረቱ ከሆነ ከመከፋፈሉ በፊት በነበረው የድርጅትና የንግድ ስም የሚጠቀምበት ክፋይ አካል የትኛው እንደሆነ ከመከፈሉ በፊት በነበሩት ሙሉ አባላት የተፈረመ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ቃለ-ጉባኤ መቅረብ አለበት፤
4. የተከፈሉት አካላት የአባላት ዝርዝር፣ ካፒታል፣ የድርጅት ስም፣ የንግድ ስም እና የመሳሰሉት ስለንግድ ኩባንያዎች በንግድ ህጉ፣በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ደንብና መመሪያ የተጻፉት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

55. የንግድ ማህበር ህጋዊ አቋም ስለመለወጥ

ማናቸውም የንግድ ማህበር ህጋዊ አቋሙን ሲለውጥ፦

1. የንግድ ማህበሩ ወደ ሌላ የንግድ ማህበርነት መለወጥ በንግድ ህጉ መሰረት የህጋዊ የሰውነት መብቱን እንዲያጣ የማያደርገው ሲሆን የሶስተኛ ወገኖችን ከተለወጠው የንግድ ማህበር መብታቸውን ወይም ጥቅማቸውን ማስከበር ይችላሉ፤
2. የንግድ ማህበራት ህጋዊ አቋማቸውን ሲለውጡ ለውጡን ለመስማማታቸው በሙሉ አባላት የተፈረመ እና ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ ቃለጉባኤ ማቅረብ አለባቸው፤
3. የተለወጠው የንግድ ማህበር ረቂቅ የመመስረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ለመዝጋቢው አካል መቅረብ አለበት፤
4. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በተለወጠው የንግድ ማህበር ስም እና ህጋዊ አቋም እንዲያወጡ መዝጋቢው አካል ደብዳቤ በመላክ የተለወጠው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዲቀርብ ያደረጋል፣
5. የተለወጠው የንግድ ማህበር የፀደቀ የመመስረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ለመዝጋቢው አካል ማቅረብ አለበት፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archiver
መዝገብ ቤት

6. የቀድሞው የንግድ ማህበር የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፈቃዶች ተሰውጠው በተሰወጠው የንግድ ማህበር ህጋዊ አቋም በአዲስ መልክ እንዲሰጥ ይደረጋል፤

7. ሌሎች የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ድንጋጌዎች ለዚህም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

56. ስለንግድ ወኪል

ማንኛውም የንግድ ወኪል፡-

1. ወካዩ ከሚገኝበት ሀገር ህጋዊ የሰውነት ማረጋገጫ ያለው መሆኑን እና በሚወክለው የስራ መስክ ላይ የተሰማራ ስለመሆኑ የሚያሳይ ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ሰነድ ማቅረብ አለበት፣

2. ለተወካዩ በአዋጁ አንቀፅ 39 መሰረት የውክልና ስልጣን የተሰጠበት ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ ሰነድ መቅረብ አለበት፤

3. የንግድ ስራ ፈቃድን ስለመስጠት፣ ስለማደስ፣ ስለማሻሻል፣ ስለምትክ እና ስለስረዛ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ለዚህም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

57. በአዋጁ አንቀጽ 16 መሰረት የድርጅት ስም ወይም የንግድ ስም አፈፃፀም

1. በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ1(ሀ) መሰረት" የንግድ ስም ወይም የድርጅት ስም አንድ አይነት ወይም በሚያሳስት ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ" የሚለው አፈፃፀም ተመሳሳይ መሆን አሳሳች ከመሆን ጋር አብሮ መምጣት ይኖርበታል።"ተመሳሳይ" መሆኑ ብቻ ወይም "አሳሳች" መሆኑ ብቻ እንዳይመዘገብ አይከለክልም፤

2. በመዝጋቢው መስሪያ ቤት ያልተመዘገቡ ሀገር አቀፍ ወይም አለምአቀፍ እውቅና ያላቸው የድርጅት ስሞች ለሌሎች የንግድ ድርጅቶች ተሰጥተው ከተገኙ ይህም በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን የንግድ ድርጅት ስሙን እንዲቀየር ስሙን እየተጠቀመበት ላለው ነጋዴ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያስተካክል ደብዳቤ ይሰጠዋል። በዚህ ጊዜ ገደብ ካላስተካከለ ስሙ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤

3. ማንኛውም ነጋዴ በድርጅት ስም ያስመዘገበውን ስም በሌላ እስካልተያዘና መስፈርቶችን እስካሟላ ድረስ በንግድ ስምነት መጠቀም ይችላል፤

4. ማንኛውም ነጋዴ በንግድ ስምነት የተያዘ ስምን በድርጅት ስምነት እስካልተያዘ ጊዜ ድረስ መስፈርቶቹን አሟልቶ በድርጅት ስምነት መጠቀም ይችላል፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

5. የድርጅት እና የንግድ ስሞችን በማጣራት ሂደት ስሞቹን የሚያጣራው ባለሙያ ውሳኔ ላይ ተገልጋዩ ካልተስማማ ቅሬታውን ለቡድን መሪው በማቅረብ ይወሰናል፤ ተገልጋዩ በቡድን መሪው ውሳኔ ካልተስማማ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ስራን የሚያስተባብሩ ኃላፊዎች ውሳኔ የመጨረሻው ይሆናል፤የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ በዚህ ንዑስ አንቀፅ በተጠቀሱ በተመሳሳይ ደረጃ በሚገኙ ኃላፊዎች ውሳኔ ይሰጣል፤
6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 መሰረት ውሳኔ ሰጪ አካላት መቃወሚያቸውን ወዲያውኑ በፅሁፍ ለተገልጋዩ ይሰጣሉ፤
7. የድርጅት ስም ወይም የንግድ ስም አፈፃፀም ዝርዝር ማብራሪያ በአባሪ-III ተያይዞ ይገኛል።

58. የመተባበር ግዴታ

1. የውጭ ድህረ-ፈቃድ ተቆጣጣሪ አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ማንኛውንም ዓይነት መረጃዎች ፎቶ ኮፒ በማድረግ፣ ፎቶ ግራፍ በማንሳት ወይም መረጃዎችን በመረጠው መንገድ ለመውሰድ እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፣
2. ይህን መመሪያ ለማስፈፀም ሁሉም አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፤
3. ይህን መመሪያ በማስፈፀም ሂደት በተለየ ሁኔታ የፀጥታ አካላት የመተባባር ግዴታ አለባቸው።

59. የተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

በዚህ መመሪያ ከተደነገጉ ጉዳዮች ጋር ተቃራኒ የሚሆን ማንኛውም መመሪያ አሰራር ወይም ተለምዶ ተፈፃሚነት አይኖረውም፣

60. የተሻሩ መመሪያዎች

የንግድ ስምን ስለማጣራት የወጣው መመሪያ ቁጥር 003/2007 በዚህ መመሪያ ተሸሯል።

61. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ -------- ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

2 9 ሚያዚያ 2009

በቀለ ቡላዶ (ዶ/ር)
ሚኒስትር

ዶ/ር በቀለ ቡላዶ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሚኒስትር



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archiver
መዝገብ ቤት

# አባሪ | የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መጠየቂያ የማመልከቻ ቅፆች



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

2. አባሪ

ሀ. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሰርተፊኬት ኮፒ

ለ. የንግድ ቤቱ የአመልካች ንብረት ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ፣ የኪራይ ከሆነ ሰነድን ለማረጋገጥ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የኪራይ ውል ወይም ከአካባቢ መስተዳድር የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ

ሐ. የአመልካች የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ/ የጸና ፓስፖርት ፎቶኮፒ/

መ. አመልካቹ 6 ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተነሳው 2 ፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶ ግራፍ

ሠ. የንግድ ምዝገባው የተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን መመለስ

ረ. የጠፋ ከሆነ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

አመልካቹ የንግድ ማህበር ከሆነ ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ፤

ሀ. የፀደቀ መመሥረቻ ፅሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጅ፣

ለ. አክሲዮን ማህበር ከሆነ ተፈርሞ የፀደቀው ካፒታል አንድ አራተኛ (¼ ) በባንክ ዝግ ሂሳብ ተቀማጭ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ፣

ሐ. የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም ማናቸውም የንግድ ዓላማ ያለው በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ሌላ ተቋም ከሆነ የተቋቋመበትን አዋጅ ወይም ደንብ እንዲሁም የሥራ አስኪያጁን የሹመት ደብዳቤ ማቅረብ፤

መ. የውጭ ሀገር ዜጋ/ማህበር ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና የግለሰቡ የታደሰ ፓስፖርት እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶኮፒ ማቅረብ አለበት፡፡

ማረጋገጫ

በዚህ ማመልከቻ ቅጽ ውስጥ የተሞሉትና በአባሪ አያይዤ ያቀረብኳቸው ማስረጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካቹ ሙሉ ስም________________________.

ፊርማ____________________________.

ቀን_____________________________.

---

**ለመ/ቤቱ አገልግሎት ብቻ**

ከላይ የቀረበው ማመልከቻ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 መሰረት ትክክለኛ እና መረጃዎች የተሟሉ ስለሆነ ብር ____________________ ከፍለው አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጌአለሁ፡፡

ያረጋገጠው ባለሙያ ሙሉ ስም______________________.

ፊርማ__________________

ቀን___________________

ሌላ ከሆነ ይገለጽ ______________________________

መ. ምትክ  የጠፋ ☐  የተበላሸ ☐

ሠ. ስረዛ ☐

የሚሰረዘው የንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር______________,__________,______________,

የተመለሰው ንግድ ስም ______________________ የንግድ ስም ቁጥር______________

2. አባሪ

ሀ. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሰርተፊኬት ኮፒ

ለ. የንግድ ቤቱ የአመልካች ንብረት ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ፣ የኪራይ ከሆነ ሰነድን ለማረጋገጥ ስልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ የኪራይ ውል ወይም ከአካባቢ መስተዳድር የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ

ሐ. የአመልካች የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ/ የጸና ፓስፖርት ፎቶኮፒ/

መ. አመልካቹ 6 ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተነሳው 2 ፓስፖርት መጠን ያለው ጉርድ ፎቶ ግራፍ

ሠ. የንግድ ፈቃድ የተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን መመለስ

ረ. የጠፋ ከሆነ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ አለበት

ሰ. የተጠየቀው የስራ መስክ የብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ማቅረብ

ሸ. ለዕድሳት የግብር ክሊራንስ

አመልካቹ የንግድ ማህበር ከሆነ ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ

ሀ. የፀደቀ መመሥረቻ ፅሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ፣

ለ. አክሲዮን ማህበር ከሆነ ተፈርሞ የጸደቀው ካፒታል አንድ አራተኛ (¼ ) በባንክ ዝግ ሂሳብ ተቀማጭ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ፣

ሐ. የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም ማናቸውም የንግድ ዓላማ ያለው በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ሌላ ተቋም ከሆነ የተቋቋመበትን አዋጅ ወይም ደንብ እንዲሁም የሥራ አስኪያጁን የሹመት ደብዳቤ ማቅረብ፤

መ. የውጭ ሀገር ዜጋ/ማህበር ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና የግለሰቡ የታደሰ ፓስፖርት እና አስፈላጊ ገፆች ፎቶኮፒ ማቅረብ አለበት።

ማረጋገጫ

በዚህ ማመልከቻ ቅጽ ውስጥ የተሞሉትና በአባሪ አያይዤ ያቀረብኳቸው ማስረጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

የአመልካቹ ሙሉ ስም______________________.

ፊርማ______________________.

ቀን______________________.

---

<u>ለመ/ቤቱ አገልግሎት ብቻ</u>

ከላይ የቀረበው ማመልከቻ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 መሰረት ትክክለኛ እና መረጃዎች የተሟሉ ስለሆነ ብር ______________________ ከፍለው አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጌአለሁ።

ያረጋገጠው ባለሙያ ሙሉ ስም ______________________

ፊርማ______________________.

ቀን ______________________



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

ሸ. ለጠፋበት ምዝገባ/ልዩ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ

ቀ. የተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን ምዝገባ/ልዩ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ

ማረጋገጫ

በዚህ ማመልከቻ ቅጽ ውስጥ የተሞሉትና በአባሪ አያይዤ ያቀረብኳቸው ማስረጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

የአመልካቹ ሙሉ ስም_______________.

ፊርማ_______________.

ቀን_______________.

---

**ለመ/ቤቱ አገልግሎት ብቻ**

ከላይ የቀረበው ማመልከቻ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 መሰረት ትክክለኛ እና መረጃዎች የተሟሉ ስለሆነ ብር _______________ ከፍለው አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጌአለሁ።

ያረጋገጠው ባለሙያ ሙሉ ስም_______________

ፊርማ_______________.

ቀን_______________



ንግድ ሚኒስቴር
Minisstry of Trade Archives
መዝገብ ቤት

**አባሪ**

ሀ. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት

ለ. አድራሻ ማረጋገጫ የራሱ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የኪራይ ከሆነ ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የኪራይ ውል

ሐ. የንግድ እንደራሴው 6 ወር ያልሞላው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶ ግራፍ

መ. $100,000 (አንድ መቶ ሺ. የአሜሪካን ዶላር) በእንደራሴው ስም ገቢ የተደረገበት የባንክ ማረጋገጫ

ሠ. ለማሻሻያ የተሰጠውን ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት እና ማሻሻያ የሚደረግባቸውን ማስረጃዎች

ረ. ለጠፋበት የምስክር ወረቀት ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ

ሸ. የተበላሸበት ከሆነ የተበላሸውን ልዩ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ

ቀ. ወካዩ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ስለመክፈቱ የወሰነበት ቃለ ጉባኤና እንደራሴው የተወከለበት የሹመት ደብዳቤ

በ. ወካዩ ድርጅት የተቋቋመበት ሕጋዊ ሰነድ

**ማረጋገጫ**

በዚህ ማመልከቻ ቅጽ ውስጥ የተሞሉትና በአባሪ አያይዤ ያቀረብኳቸው ማስረጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካቹ ሙሉ ስም____________________.

ፊርማ__________________________.

ቀን___________________________.

---

<u>**ለመ/ቤቱ አገልግሎት ብቻ**</u>

ከላይ የቀረበው ማመልከቻ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 መሰረት ትክክለኛ እና መረጃዎች የተሟሉ ስለሆነ ብር ____________________ ከፍለው አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጌአለሁ፡፡

ያረጋገጠው ባለሙያ ሙሉ ስም__________________

ፊርማ__________________________.

ቀን___________________________



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

**አባሪ**

ሀ. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት

ለ. አድራሻ ማረጋገጫ የራሱ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የኪራይ ከሆነ ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የኪራይ ውል

ሐ. የንግድ እንደራሴው 6 ወር ያልሞላው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶ ግራፍ

መ. ለእድሳት የግብር ክሊራንስ እና የሚታደሰው ልዩ የምስክር ወረቀት

ሠ. $100,000 (አንድ መቶ ሺ. የአሜሪካን ዶላር) በእንደራሴው ስም ገቢ የተደረገበት የባንክ ማረጋገጫ

ረ.ማሻሻያ ከሆነ የተሰጠውን ልዩ ምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ እና ማሻሻያ የሚደረግባቸውን ማስረጃዎች

ሰ.የምስክር ወረቀት ለጠፋበት ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ

ሸ. የተበላሸበት ከሆነ የተበላሸውን ልዩ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ

ቀ. የእንደራሴው ለውጥ ከሆነ በቀድሞው እንደራሴው ስም የተሰጠውን ልዩ የምስክር ወረቀት እና የመዝጊያ ክሊራንስ

**ማረጋገጫ**

በዚህ ማመልከቻ ቅጽ ውስጥ የተሞሉትና በአባሪ አያይዤ ያቀረብኳቸው ማስረጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካቹ ሙሉ ስም ____________________.

ፊርማ ____________________.

ቀን ____________________.

---

<u>ለመ/ቤቱ አገልግሎት ብቻ</u>

ከላይ የቀረበው ማመልከቻ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 መሰረት ትክክለኛ እና መረጃዎች የተሟሉ ስለሆነ ብር ____________________ ከፍለው አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጌአለሁ፡፡

ያረጋገጠው ባለሙያ ሙሉ ስም ____________________

ፊርማ ____________________.

ቀን ____________________



Ministry of Trade Archives

**አባሪ**

ሀ. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት

ለ. አድራሻ ማረጋገጫ የራሱ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ፣ የኪራይ ከሆነ ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የኪራይ ውል

ሐ. አመልካቹ 6 ወር ያልሞላው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶ ግራፍ

ረ. ማሻሻያ ከሆነ የተሰጠውን ልዩ ምስክር ወረቀት እና ማሻሻያ የሚደረግባቸውን ማስረጃዎች

ሰ. የምስክር ወረቀት ለጠፋበት ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ

ሸ. የተበላሸበት ከሆነ የተበላሸውን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ

**ማረጋገጫ**

በዚህ ማመልከቻ ቅጽ ውስጥ የተሞሉትና በአባሪ አያይዤ ያቀረብኳቸው ማስረጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካቹ ሙሉ ስም_______________________.

ፊርማ_______________________.

ቀን_______________________.

---

**ለመ/ቤቱ አገልግሎት ብቻ**

ከላይ የቀረበው ማመልከቻ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 መሰረት ትክክለኛ እና መረጃዎች የተሟሉ ስለሆነ ብር _______________________ ከፍለው አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጌአለሁ፡፡

ያረጋገጠው ባለሙያ ሙሉ ስም_______________________

ፊርማ_______________________.

ቀን_______________________



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archive

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የንግድ ሚኒስቴር

አባሪ | ቅፅ 08

______ቀን____ወር____ዓ.ም

## አዲስ የጠረፍ ንግድ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት የእድሳት/ የማሻሻያ/ የምትክ እና የስረዛ መጠየቂያ ቅጽ

1. አመልካች

   ግለሰብ ሙሉ ስም ____________________

   ዜግነት ________ እድሜ____________ ፆታ ________

   ማህበር ከሆነ የማህበሩ ሥም ____________________

2. አድራሻ፡-

   ሀ. የመኖሪያ አድራሻ:- ክልል__________ ከተማ __________ ዞን/ክፍለ-ከተማ __________

   ወረዳ____________________ ቀበሌ __________ የቤት/ቁ ______________

   ስልክ ቁጥር ________________ ሞባይል __________ ፋክስ __________

   ፖ.ሳ.ቁ ________________ ኢ.ሜይል ____________________

   ለ. የሥራ አድራሻ:- ክልል__________ ከተማ __________ ዞን/ክፍለ-ከተማ __________

   ወረዳ____________________ ቀበሌ __________ የቤት/ቁ ______________

   ስልክ ቁጥር የቢሮ ________________ ሞባይል __________ፋክስ __________

   ፖ.ሳ.ቁ ________________ ኢ.ሜይል ____________________

3. ካፒታል

   ለንግድ ስራው የተመዘገበው ካፒታል መጠን በብር ______

4. የአገልግሎት አይነት (✓ ያድርጉ)

   ሀ. አዲስ የጠረፍ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ☐ ለ.እድሳት ☐

   ሐ. ማሻሻያ ☐
   (በዝርዝር ይገለፅ) ____________________

   መ. ምትክ የጠፋ ☐ የተበላሸ ☐
   የጠፋው (የተበላሸው) የጠረፍ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቁጥር__________

   ሠ. ስረዛ ☐

   የሚሰረዘው የጠረፍ ልዩ የንግድ ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቁጥር______________



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

**አባሪ**

ሀ. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የምስክር ወረቀት

ለ. አድራሻ ማረጋገጫ የራሱ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የኪራይ ከሆነ ሰነድን ለማረጋገጥ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ የኪራይ ውል

ሐ. አመልካቹ 6 ወር ያልሞላው ሁለት ፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶ ግራፍ

መ. ማሻሻያ ከሆነ የተሰጠውን የጠረፍ ንግድ ሥራ ፈቃድ ልዩ ምስክር ወረቀት እና ማሻሻያ የሚደረግባቸውን ማስረጃዎች

ሠ. የጠረፍ ንግድ ሥራ ፈቃድ ልዩ ምስክር ወረቀት ለጠፋበት ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ማቅረብ

ረ. የተበላሸበት ከሆነ የተበላሸውን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ

ሰ. የአመልካች የታደሰ መታወቂያ/ ፓስፖርት/ ኮፒ

ሸ. የጠረፍ ንግድ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚመለከተው አካል የጠረፍ ንግድ እንዲነግድ የተፈቀደለት ስለመሆኑ የሚገልጽ የጽሁፍ ማረጋገጫ

ቀ. የጠረፍ ንግድ ከሚካሄድበት አካባቢ አስተዳደር ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለውና ነዋሪ ስለመሆኑ የሚገልጽ ማረጋገጫ

**ማረጋገጫ**

በዚህ ማመልከቻ ቅጽ ውስጥ የተሞሉትና በአባሪ አያይዤ ያቀረብኳቸው ማስረጃዎች በሙሉ ትክክል መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካቹ ሙሉ ስም________________________.

ፊርማ________________________________.

ቀን_________________________________.

---

**ለመ/ቤቱ አገልግሎት ብቻ**

ከላይ የቀረበው ማመልከቻ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 መሰረት ትክክለኛ እና መረጃዎች የተሟሉ ስለሆነ ብር ________________________ ከፍለው አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጌአለሁ፡፡

ያረጋገጠው ባለሙያ ሙሉ ስም____________________

ፊርማ________________________________.

ቀን_________________________________

Ministry of Trade Archives
መዝገብ ቤት

# አባሪ II የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የምስክር ወረቀቶች



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

Annex II Form 06

አባሪ II ቅጽ 06

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ
ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድ ሚኒስቴር

The Federal Democratic Republic
Of Ethiopia
Ministry of Trade

ፎቶ

የመዝገብ ቁጥር/Fill No ____________

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/TIN ____________

የንግድ ምዝገባ ቁጥር ____________

Principal Registration No
የቀድሞው የምዝገባ ቁጥር ____________

Principal Registration date
የቀድሞው የምዝገባ ቀን ____________

First Registration Date
መጀመሪያ የተመዘገበበት ቀን ____________

## የዘርፍ ማኅበራት ንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት
## በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር
## 980/2008 መሠረት የተሰጠ

1. የዘርፍ ማኅበራት ስም ____________
2. ዜግነት ____________
3. የፕሬዝዳንቱ ስም ____________
4. የንግድ ድርጅቱ አድራሻ

   ክልል ____________ ዞን/ክፍለ ከተማ ____________

   ከተማ ____________ ወረዳ ____________

   ቀበሌ ____________ የቤት ቁጥር ____________

   ፖ.ሳ.ቁ ____________ ስልክ ቁጥር ____________

   ፋክስ ____________ ኢ-ሜል ____________
5. ካፒታል በኢ.ት.ብር ____________

   የተሰማራባቸው ዘርፎች ____________

   በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ____________ የተመዘገበ መሆኑን እናረጋግጣለን።

   ይህ የንግድ የምስክር ወረቀት ዛሬ ____________ ዓ.ም

   በ____________ ተሰጠ።

## Certificate of Commercial Registration of sectorial Association
## Issued under Commercial Registration and Business license Proc No. 980/2016

1. Sectoral Association Name ____________
2. Nationality ____________
3. President Name ____________
4. Business Address

   Region ____________ Zone/Sub City ____________

   City ____________ Woreda ____________

   Kebele ____________ House No. ____________

   P.O.Box ____________ Tel. No ____________

   Fax ____________ E-Mail ____________
5. Capital in ETB ____________
6. Type of activities engaged ____________

   Has duly been registered under TIN ____________

   This Registration Certification is issued in ____________

   This day ____________

| የኃላፊ ስም ____________ | ማህተም ____________ | ፊርማ ____________ |
|---|---|---|
| Official's Name | Seal | Signature |

Ministry of Trade Archives
መዝገብ ቤት

# አባሪ III የድርጅት እና የንግድ ስም ማብራሪያ



Ministry of Trade Archives
መዝገብ ቤት

## የድርጅት እና የንግድ ስም ምዝገባ ማብራሪያ

የድርጅት እና የንግድ ስም ምዝገባ የሚከናወነው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 16 መሰረት ነው፡፡ በአዋጁ መሰረት ማንኛውም በንግድ ሥራ ሊሰማራ የሚፈልግ ሰው በንግድ መዝገብ በሚመዘገቡበት ቦታ የንግድ ስሙን ማስመዝገብ ይኖርበታል፡፡

## የድርጅት እና የንግድ ስም ዓላማ

የድርጅትና የንግድ ሥም ምዝገባን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ዓላማ በሦስት መልኩ የሚታይ ነው፡፡

- አንደኛው እንዲመዘገብ የተጠየቀው ሥም ቀደም ብለው ከተመዘገቡ የንግድ ሥሞች ጋር አንድ ዓይነት ወይም በሚያሳስት ደረጃ ተመሳሳይ እንዳይሆን ማድረግ ነው፡፡
- ሁለተኛው ደግሞ ሕብረተሰቡ በንግድ ስሙ አማካኝነት ስለንግዱ የተሳሳተ መረጃ እንዳይወስድ ማድረግ ነው፡፡
- ሶስተኛው ዓላማ ደግሞ የንግድ ስሙ ከሞራል ወይም ሥነ- ምግባር ተቃራኒ እንዳይሆን መቆጣጠር ነው፡፡

እነዚህ ሦስት ዓላማዎች በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጁ የንግድ ሥም ድንጋጌዎች ላይ በተለያየ መልኩ ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ የንግድ ስምን የሚመለከቱት የአዋጁ ዋና ዋና ድንጋጌዎችን ከዚህ በታች ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

1. በአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ስም ቀደም ብሎ ከተመዘገቡት የንግድ ሥሞች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች መሆን የለበትም፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ለምዝገባ የቀረበው ሥም ቀደም ብለው ከተመዘገቡ የንግድ ስሞች ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች ሊሆን አይገባም፡፡



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

ሀ. ቀደም ብለው ከተመዘገቡ ሥሞች ጋር አንድ ዓይነት ያልሆነ፤

አንድ ነጋዴ ቀደም ብሎ ከተያዘ የንግድ ሥም ጋር አንድ ዓይነት ስም ማስመዝገብ አይችልም። ምክንያቱም፡-

- ስሙ የንግዱን ዓይነት በግልፅ የማይለይ በመሆኑና ይህም በተለያዩ የንግድ አይነቶች ማንነት ላይ መደናገርን ስለሚፈጥር ፤
- ሕብረተሰቡ ስሙ የትኛውን ንግድ እንደሚያመለክት ለማወቅ ሲቸገር ስለሚችል፤
- ንግዱ በአስፈፃሚ አካላት በቀላሉ የሚለይበት ስም ሊኖረው ስለሚገባ ነው።

የቀረበው የንግድ ሥም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለመሆኑ ብዙ አስቸጋሪ ሆኖ አይታይም። እንዲመዘገብ የተጠየቀው ሥም በንግድ ሥም መዝገቦች ላይ መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ብቻ የሚጠይቅ ነው።

ይህንን ድንጋጌ በተመለከተ ሁለት ጉዳዮች ግልፅ ሊሆኑ ይገባል።

- አንደኛው ምዝገባውን ለመከልከል አዲሱ ሥም በማንኛውም ሁኔታ ቀደም ብሎ ከተመዘገበው ስም ጋር አንድ ዓይነት(identical) መሆን ይኖርበታል። ማለትም በሁለቱ ስሞች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት ሊኖር አይገባም።
- ሁለተኛው ጉዳይ ቀደም ብሎ የተመዘገበው ስም በስራ ላይ ያለ ወይም በተለያዩ ምክንየቶች ያልተሰረዘ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል።

የነጋዴው የንግድ ምዝገባ ሲሰረዝ የተመዘገበው የንግድ ስም መሰረዝ ይኖርበታል። ይህም ማለት አንድ የንግድ ስም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ሥም ጋር አንድ ዓይነት መሆኑን ለመወሰን የምንመለከተው ሥራ ላይ ያሉ ነጋዴዎችን የንግድ ስሞች ብቻ ነው።

በተለያዩ ምክንያቶች ከተሰረዙ የንግድ ስራ ፈቃዶች ጋር የተያያዙ የንግድ ሥሞችን መመልከት አይኖርብንም።



Ministry of Trade
Archives

**ለ. ቀደም ብለው ከተመዘገቡ ስሞች ጋር ተመሳሳይና አሳሳች ያልሆነ**

እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም ቀደም ብሎ ተመዝግቦ በሥራ ላይ ካለ ሌላ የንግድ ስም ጋር ሙሉ በሙሉ አንድ ዓይት ባይሆንም "ተመሳሳይና አሳሳች" ሊሆን ይችላል፡፡ አዲሱ የንግድ ስም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ሌላ የንግድ ሥም ጋር ተመሳሳይና አሳሳች ሆኖ ከተገኘ በንግድ ሥምነት ሊመዘገብ አይችልም፡፡

ወደ ዝርዝር ከመገባቱ በፊት መታወቅ ያለበት ጉዳይ በዚህ ድንጋጌ የተከለከለው ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር "ተመሳሳይ" ብቻ ሳይሆን "አሳሳችም" መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህም ማለት እንዲመዘገብ የቀረበው የንግድ ሥም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር "ተመሳሳይ" በመሆኑ ብቻ ምዝገባ አይከለከልም፡፡ "ተመሳሳይ" ቢሆንም "አሳሳች" ላይሆን ይችላልና፡፡

አንድ የንግድ ሥም ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር "ተመሳሳይና አሳሳች" (confusingly similar) የሚሆነው መቼ ነው? የሚለው ጥያቄ በንግድ ምዝገባ ሥርዓቱ ወሳኝ የሆነ ነገር ግን ቁርጥ ያለ መልስ ሊሰጥበት የማይችል ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ መወሰን የሚኖርበት የሚቀርቡትን ሥሞች በማወዳደር፣ በመመርመርና በማገናዘብ በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ እንደ ሁኔታው (on a case -by-case- basis) ነው፡፡

በአጠቃላይ ግን አንድ የንግድ ሥም ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር "ተመሳሳይና አሳሳች" ነው የሚባለው ሁለቱ ሥሞች ከመቀራረባቸው የተነሳ ሕብረተሰቡ አንዱን ሥም ከሌላው ጋር በማምታታት ሊሳሳት ይችላል ተብሎ ሲታመን ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ስም ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር "ተመሳሳይ እና አሳሳች" መሆኑን ለመወሰን መጀመሪያ "ተመሳሳይ" መሆኑን መወሰን ያስፈልጋል፡፡ "ተመሳሳይ" መሆናቸው ከተወሰነ በኋላ ደግሞ "አሳሳች" መሆናቸውም መወሰን ይኖርበታል፡፡

እነዚህን ጉዳዮች ለመወሰን የተለያዩ ማነጻጸሪያዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፡-

ሀ/ የሁለቱ ሥሞች ቃላት ቅርርብነት፣

ለ/ የሁለቱ ሥሞች አነባበብ ቅርርብነት፣



Ministry of trade Archives
መዝገብ ቤት

ሐ/ የሁለቱ ሥሞች ትርጉም ቅርርብነት እና

መ/ ሁለቱ ሥሞች የሚወክሏቸው የንግድ ዓይነቶች ቅርርብነት ናቸው።

ሀ. በሁለቱ ሥሞች ላይ የሚገኙት ቃላት ቅርርብነት

አንድ ለምዝገባ የቀረበ ሥም ላይ የተጠቀሱት ቃላት ተመዝግቦ በሚገኝ ሌላ የንግድ ስም ላይ ከሚገኙ ቃላት ጋር አንድ ዓይነት ባይሆኑም እጅግ ተቀራራቢ በመሆናቸው አሳሳች ሊሆኑ ይችላሉ።

- ቀድሞ በተመዘገበ ሥም ላይ ቅጽሎችን መጨመር

ለምሳሌ ፦ ሕብረት ቡና ንግድ ተብሎ የተመዘገበ የንግድ ስም ቢኖር፤

- የሕብረት ቡና ንግድ
- ሕብረት ቡና ንግድ ቁ. 2
- ሕብረት የቡና ንግድ
- የሕብረት የቡና ንግድ
- ሕ- ብ- ረ-ት ቡና ንግድ
- ሕብ-ረት ቡና ንግድ
- ሕብረቶች ቡና ንግድ ወዘተ ተመሳይና አሳሳች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ።

ነገር ግን የአንድ ፊደል ለውጥ ሁለቱን ስሞች ሙሉ በሙሉ ሊለውጥ ይችላል።

ለምሳሌ፦ "ጥረት የድለላ ስራ" እና "ጥራት የድለላ ስራ" ሙሉ በሙሉ የተለያዩ ስሞች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ተመዝግቦ በሚገኝ ሥም ላይ ሌላ ሙሉ ቃል ቢጨመርበት ተመሳሳይና አሳሳች ሊባል አይችልም።

ለምሳሌ፦ እድገት በህብረት ቡና ንግድ

ሕብረት ለሥራ ቡና ንግድ

ሕብረት ለእድገት ቡና ንግድ ወዘተ የሚሉ የንግድ ስሞች"ሕብረት ቡና ንግድ" ተብሎ ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ንግድ ስም ጋር "ተመሳሳይና አሳሳች" ናቸው ማለት አይቻልም።



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

- የቃላትን ቅደም ተከተል መቀያየር

አንዳንድ ጊዜ ቀደም ብሎ የተመዘገበ ሥም ላይ የሚገኙ ቃላትን ቅደም ተከተል በመለዋወጥ የሚቀርብ የንግድ ስም ምዝገባ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ አዲሱ የንግድ ሥም ቀደም ሲል የተመዘገበውን የንግድ ሥም ቃላት በምን ያህል ደረጃ ቅደም ተከተላቸውን በመቀያየር አሳሳች እንዳይሆን አድርጓል የሚለው መታየት ይኖርበታል፡፡

ለምሳሌ፡-"ሕብረት የቡናና ሻይ ንግድ" የሚል ቀደም ብሎ የተመዘገበ የንግድ ሥም ቢኖር እና "ሕብረት የሻይና ቡና ንግድ" የሚል የንግድ ስም ለምዝገባ ቢቀርብ የተደረገው የቃላት ቅደም ተከተል መጠናኛና በአጠቃላይ በንግድ ስሙ ላይ ጎልቶ የወጣ ልዩነት የማያመጣ በመሆኑ "ተመሳሳይና አሳሳች" ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የተደረገው የቃላት ቅደም ተከተል ለውጥ ከፍተኛ በመሆኑ በሁለቱ የንግድ ሥሞች መካከል የሚኖረው ልዩነት በግልፅ የሚታይ ሲሆን በሚችልበት ጊዜ አዲሱ የንግድ ስም ቀድሞ ከነበረው የንግድ ስም ጋር ተመሳሳይና አሳሳች አይደለም ተብሎ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

ለምሳሌ፡- ሲስተም ኤሌክትሮኒክስ ንግድ እና ኤሌክትሮኒክስ ሲስተም ንግድ ተመሳሳይና አሳሳች ላይባሉ ይችላሉ፡፡

**የግለሰብ ስም የንግድ ስም ሆኖ መመዝገብ**

የግለሰብ ስሞች የንግድ ስም ሆነው ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ተመሳሳይ የግል ስሞች በመኖራቸው አንድ ነጋዴ ስሙን በንግድ ስምነት ካስመዘገበው ሌላ ነጋዴ የራሱ ስም ቢሆንም በንግድ ስምነት ለመጠቀም ቀድሞ ከተመዘገበ የንግድ ስም ጋር አንድ ዓይነት ነው ተብሎ ሊከለከል ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ በተቻለ መጠን ከተመዘገበው የንግድ ሥም ሊለይ የሚችለበትን ጭማሪ በማድረግ ለመመዝገብ መሞከር ያስፈልጋል፡፡



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade

ለምሳሌ፡ "ወንድወሰን - የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ" የሚል የተመዘገበ የንግድ ስም ቢኖር ስሙ ወንድወሰን የሆነ ሌላ ነጋዴ ተመሳሳይ ስም ለተመሳሳይ የንግድ ሥራ ሊያስመዘግብ አይችልም፡፡ ይሁንና በስሙ ላይ ተጨማሪ ስም ወይም ቃል በመጨመር ሊመዘገብ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

ለምሳሌ፡-

- ወንድወሰን ቶላ ጉርሜ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ
- ወንድወሰን ቶላ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ
- ወንድወሰን 8798 የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ ወዘተ የሚሉት የንግድ ስሞች ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ አንደኛ አንድ አይነት የግለሰብ ስሞች ለተለያዩ የንግድ ሥራዎች የንግድ ስም ሆነው ሊመዘገቡ ይችላሉ ምክንያቱም በዚህ ጊዜ አሳሳች ሊሆኑ ስለማይችሉ ነው፡፡

ለምሳሌ፡ "ወንድወሰን የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ንግድ" የሚለው የንግድ ስም ቢኖርም "ወንድወሰን ፍራፍሬ ንግድ"፣ "ወንድወሰን ጨርቃጨርቅ ንግድ" ወዘተ የሚሉ የንግድ ስሞች ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

ሁለተኛው ፆታን ገላጭ ስሞች አንድ ዓይነት ስሞች ወይም "ተመሳሳይና አሳሳች" ላይሆኑ ይችላሉ፡

ለምሳሌ፡-

- ታደለ እና ታደለች
- ዘነበ እና ዘነበች
- አበበ እና አበበች
- ተሾመ እና ተሾመች ወዘተ ሁል ጊዜ አንድ ዓይነት ወይም "ተመሳሳይና አሳሳች" ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም፡፡



Archives
መዝገብ ቤት

### ሰ. የሁለቱ ሥሞች አነባበብ ቅርርብነት

አንዳንድ ጊዜ ሊመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ሥም አፃፃፍ ቀደም ብሎ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር ልዩነት ቢኖረውም በአነባብ ግን "ተመሳሳይና አሳሳች" ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል።

ለምሳሌ፡-

- ኩልል የመጠጥ ውሃ እና ኩል የመጠጥ ውሃ
- Kool water እና Cool water
- Koka —kola እና Coka — kola
- መጋቢት 15 ልብስ ስፌት እና መጋቢት አስራ አምስት ልብስ ስፌት ተመሳሳይና አሳሳች ስሞች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ።

### ሐ.የሁለቱ ሥሞች ትርጉም ቅርርብነት

ለምዝገባ የቀረበው የንግድ ሥም ቃላቶቹ ቀድሞ ከተመዘገበ ሥም ጋር የተለያየ ቢሆንም ትርጉማቸው ግን አንድ አይነት ወይም የተቀራረበ ሊሆን ይችላል።

ለምሳሌ፡-

- አስተማማኝ ኮንስትራክሽን እና ሪላይብል ኮንስትራክሽን
- ሎያል ትራንዚት እና ታማኝ ትራንዚት

የእነዚህ ስሞች ትርጉሞቻቸው አንድ ዓይነት ወይም ተቀራራቢ ቢሆኑም በራሳቸው ሲታዩ ግን ፈፅሞ የተለያዩ ናቸው። ህብረተሰቡም ሁለቱን ስሞች ያምታታቸዋል ተብሎ አይገመትም። በመሆኑም እነዚህ ስሞች ሁል ጊዜ አሳሳች ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም።



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

መ. ሁለቱ የንግድ ሥሞች የሚወክሏቸው የንግድ ዓይነቶች ቅርርብነት

ሁለት የንግድ ስሞች ተመሳሳይና አሳሳች ሊሆኑ የሚችሉት የሚወክሏቸው የንግድ ዓይነቶች አንድ ዓይነት ወይም በጣም የተቀራረቡ ሲሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ዓይነት የንግድ ስም ለተለያዩ የንግድ ዓይነቶች ሊሰጥ ይችላል፡፡

ለምሳሌ፡- "ሞሐ የለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ" የሚል የንግድ ሥም ቢኖርም፤

- "ሞሐ የወፍጮ ንግድ ሥራ"
- "ሞሐ የልብስ ስፌት ሥራ"
- "ሞሐ ባልትና" ወዘተ የንግድ ስሞችን መመዝገብ ይችላሉ፡፡

በተመሣሣይ "አማኑኤል ፈለቀ ካፌ" የሚል የንግድ ሥም ቢኖርም፤

- "አማኑኤል ፈለቀ የእንጨት ሥራ"
- "አማኑኤል ፈለቀ ፋርማሲ"
- "አማኑኤል ፈለቀ የድለላ ሥራ" ወዘተ የሚሉ የንግድ ሥሞች ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

<u>ማጠቃለያ</u>

አንድ የንግድ ሥም ቀድሞ ከተመዘገበ የንግድ ሥም ጋር "ተመሳሳይና አሳሳች" መሆን አለመሆኑ ሁለቱን ሥሞች ከላይ በተገለፁትና በሌሎች መመዘኛዎች በማወዳደር የሚወሰን ጉዳይ ነው፡፡ በተግባር የተለያዩ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ያሉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት መወሰን ይኖርባቸዋል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) የንግድ ስሙ ቀደም ሲል ያልተመዘገበ ቢሆንም ሌሎች ነጋዴዎችን ወይም ህብረተሰቡን የሚያሳስት አለመሆኑ

እንዲመዘገብ የተጠየቀው የንግድ ስም ቀደም ብሎ ያልተመዘገበ ቢሆንም ሕብረተሰቡን ሊያሳስት የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ሊያሳስት ይችላል ተብሎ ከታመነም በንግድ ሥምነት አይመዘገብም፡፡

ሕብረተሰቡን ሊያሳስትባቸው ከሚችልበት ሁኔታዎች የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡



ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት

1. በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) እንዲመዘገብ የተጠየቀው ስም ንግዱ ያላግባብ ከመንግስት ጋር ግንኙነት እንዳለው ሊያስመስል ከቻለ ላይመዘገብ ይችላል፡፡ መንግስት የራሱን አስተዳደራዊ ተቋማት የሚሰይምበት ስሞች አሉ፡፡

ለምሳሌ፡-

- ኮሚሽን
- ኤጀንሲ
- መምሪያ
- ቢሮ
- ማዘጋጃ ቤት ወዘተ…

እነዚህ ስሞችን በንግድ ስምነት መጠቀም ህብረተሰቡ ንግዱ ከመንግስት ጋር ግንኙነት አለው ብሎ እንዲያስብ ሊያደርገው ይችላል፡፡

ለምሳሌ፡-

- ሠላም የማዳበሪያ አስመጭ ኮሚሽን
- ታታሪ የሠራተኛና አሠሪ አገናኝ ቢሮ ወዘተ አሳሳች ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

አንድ የንግድ ስም ከመመዝገቡ በፊት ከመንግስት አካላት ወይም ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ስሞች ጋር የማይመሳሰል መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለምዝገባ የተጠየቀው ስም ከመንግስት አካላት ወይም ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ስሞች ጋር ተመሳሳይ ከሆነ የምዝገባው ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ይሁንና ለዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም ሁለት ጉዳዮችን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ መዝጋቢው ስሙ ከየትኛው የመንግስት አካል ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ስም ጋር እንደሚመሳሰል ማሳየት አለበት፡፡ የመንግስት አካላት የሚጠሩበት ሥሞች ተለይተው ታውቀው ለምዝገባ የቀረበው ሥም ከእነዚህ ሥሞች ጋር ያሳስታል ተብሎ መወሰን ይኖርበታል፡፡ በኢትዮጵያ የመንግስት አካላት ሥሞች በተለያየ ጊዜ ሊለዋወጡ ይችላሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የሚታወቁት ሥሞች የሚከተሉትን ያካትታል፤



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

- ሚኒስቴር
- ኮሚሽን
- ኤጀንሲ
- ቦርድ
- ድርጅት
- የክልል መስተዳደር
- የክልል ቢሮ
- የዞን መስተዳደር
- የከተማ መስተዳድር
- ማዘጋጃ ቤት ወዘተ...

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ሥም በተመለከተ እያንዳንዱ የልማት ድርጅት የሚቋቋመው በሕግ እንደመሆኑ የልማት ድርጅቶችን ሥም ማወቅ የሚቻለው ከሚቋቋሙበት ሕግ ላይ ነው።

ሁለተኛው ጉዳይ የተጠየቀውን የንግድ ስም ምዝገባ ለመከልከል ስሙ ከመንግስት አካላት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ስም ጋር አንድ ዓይነት መሆን አይጠበቅበትም። ይልቁንም ለምዝገባ የተጠየቀው ስም ከመንግስት አካላት ስም ወይም ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ስም ጋር ተመሳሳይ ከሆነ አይመዘገብም። የዚህም ምክንያት ሕብረተሰቡ በስሞቹ ሊሳሳት ስለሚችል ነው። በመሆኑም ለምዝገባ የቀረበው ስም ከመንግስት አካላት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ስም ጋር አንድ ዓይነት ካልሆነ ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ መወሰን አለበት።

አንድ የንግድ ስም ከመመዝገቡ በፊት ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የሠራተኛ ማህበር ወይም ሌላ አይነት ማህበር ወይም የእርዳታ ድርጅት ስም ጋር ተመሳሳይ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ከአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ለ) ጋር ተመሳሳይ ነው። ይኸውም ለመመዝገብ የቀረበው ስም ከፖለቲካ ፓርቲ ወይም ከሰራተኛ ማህበራት ወይም ከዕርዳታ ድርጅቶች ሥሞች ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ሕብረተሰቡ የንግድ ድርጅቱ ከፓርቲዎች ወይም ከሠራተኛ ማህበራት ወይም ከዕርዳታ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት አለው ብለው እንዲያስቡ በማድረግ ሊያሳስቱት ይችላሉ የሚል ነው። መዝጋቢው ይህንን ውሳኔ ለመወሰን የሚመለከተው ሥም



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

ኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ስሞች ወይም ተመዝግበው የሚታወቁ የሠራተኛ ማህበራትን ስሞች ወይም የዕርዳታ ድርጅቶችን ስሞች ነው።

ለምሳሌ፡- "ፋኦ (FAO) የወተት ልማት ንግድ" የሚል የንግድ ሥም ለምዝገባ ቢቀርብ ፋኦ (Food and Agricultural Organization) ከሚባለው ተቋም ስም ጋር ተመሳሳይ ነው ሊባል ይችላል።

**በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) የታዋቂ ስዎችን ስሞች በንግድ ስምነት መጠቀም**

የታዋቂ ስዎችን ስሞች በንግድ ስምነት መጠቀም የሚገድብባቸው ሁለት ዋነኛ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። አንደኛው ህብረተሰቡ እንዳይሳሳት ለማድረግና ሁለተኛው ደግሞ ደታዋቂ ስዎችን ክብር ለመጠበቅ ሲባል ነው።

አንድ ነጋዴ የታዋቂ ሰዎችን ስም በንግድ ስምነት በመጠቀም እነዚህ ሰዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ያላቸውን መልካም ዝና ያላግባብ ለመውሰድ ሊሞክር ይችላል። ህብረተሰቡ የታዋቂ ሰዎችን ሥም የተጠቀመውን ግድ ከታዋቂው ሰው ጋር ግንኙነት ይኖረዋል የሚል እምነት ሊያድርበት ይችላል።

ለምሳሌ፡- ሀይሌ ገብረስላሴ በሩጫው ዓለም እውቅናን ያተረፈ ሰው ነው። እንዲሁም ሀይሌ በተለያዩ የንግድ ስራዎች ላይ መሰማራቱ ይታወቃል። ህብረተሰቡ ሀይሌን በሩጫ ብቻ ሳይሆን በንግድም ያውቀዋል። አንድ ነጋዴ "ሀይሌ ገብረሥላሴ ብረታብረት ንግድ" የሚል የንግድ ሥም ቢጠቀም ህብረተሰቡ ንግዱን ከሀይሌ ገብረ ስላሴ ጋር ሊያገናኘው ይችላል። በመሆኑም የንግድ ስሙን ለማስመዝገብ የኃይሌን ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

የታዋቂ ሰዎች ሥሞች በንግድ ስምነት መጠቀም የሚገደብበት ሌላው ምክንያት ደግሞ የታዋቂውን ሰው ክብር ለመጠበቅ ነው። አንድ ነጋዴ የታዋቂ ሰዎችን ወይም የሀገር መሪዎችን ስም በንግድ ስምነት መጠቀም የሚችለው ተገቢውን ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ ነው። ይህ ድንጋጌ የሚያካትታቸው "የታዋቂ ሰዎችን" እና "የሀገር መሪዎችን" ሥሞች ነው። ይሁንና "ታዋቂ ሰዎች" የሚለው የሀገር መሪዎችንም ያካትታል ምክንያቱም የሀገር መሪዎች በሕብረተሰቡ ዘንድ ታዋቂ ስለሚሆኑ ነው።

ለዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት መመለስ የሚጋባቸው ጥያቄዎች ይኖራሉ። የመጀመሪያው ጥያቄ ታዋቂ ሰዎች ወይም የሀገር መሪዎች እነማን ናቸው? የሚለው ነው። የሀገር መሪዎችን ስም በኢንተርኔትና መሰል ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ማወቅ ብዙም ላያስቸግር ይችላል። የታዋቂ



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of trade
Archives
መዝገብ ቤት

ሰዎችን ዝርዝር ግን ማግኘቱ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ውሳኔው እንደ ሁኔታው እየታየ የሚሰጥ ነው፡፡ ሰዎች ከሌሎች በተለየ መልኩ ታዋቂ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በፖለቲካ፣ በስፖርት፣ በሥነ-ፅሁፍ፣ በሙዚቃ ወዘተ ሰዎች በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ታዋቂነትን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ እዚህ ላይ ሊታወቅ የሚገባው ጉዳይ ግን ስሙ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታወቅ ሰው ስም መሆን ይኖርበታል፡፡ በሌላ አገላለፅ ሰውየው በአማካኝ ኢትዮጵያዊ የሚታወቅ መሆን ይኖርበታል፡፡ ኔልሰን ማንዴላ፣ ባራክ ኦባማ፣ አበበ ቢቂላ፣ ጥላሁን ገሠሠ፣ ማይክል ጃክሰን፣ ወዘተ አማካኝ ንቃተ ሕሊና ላለው ኢትጵያዊ የሚታወቁ ሥዎች ናቸው፡፡ ታዋቂነቱም በሀገር ዐቀፍ ደረጃ መሆን ይኖርበታል፡፡

ድንጋጌው በየአካባቢው የሚታወቁ ሰዎችን የሚያካትት ከሆነ ለአፈፃፀም እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በመሆኑም መካተት የሚኖርባቸው በብሔራዊ ደረጃ ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን ሥሞች መሆን ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ ቀነኒሳ በቀለ በብሔራዊ ደረጃ የሚታወቅ ሰው ነው፡፡ በአንድ ወረዳ ወይም ቀበሌ የሚታወቅን ሰው ሥም ድንጋጌው ማካተት የለበትም፡፡ በዚህ መሰረት እንደ ሁኔታው የሚለዩ ታዋቂ ሰዎች ሥምን ለንግድ ሥምነት ለመጠቀም "ተገቢ ፈቃድ" መገኘት ይኖርበታል፡፡ ይህም ማለት ታዋቂው ሰው ሥሙ በንግድ ሥምነት እንዲያገለግል ግልፅ የሆነ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ አመልካቹ የታዋቂ ሰው ሥም በንግድ ሥምነት ለመጠቀም ፈቃድ ማግኘቱን ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሌላው መነሳት ያለበት ጥያቄ ድንጋጌው በህይወት የሌሉ ታዋቂ ሰዎችን ወይም የሀገር መሪዎች ሥምን ያካትታል ወይስ በሕይወት ላሉት ብቻ የተወሰነ ነው? የሚለው ነው፡፡ በአንዳንድ ሀገሮች ታዋቂ ሰዎች በህይወት የሌሉ ከሆነ ከወራሾቻቸው ፈቃድ እንዲሰጥ ይጠየቃል፡፡ ታዋቂ ሰዎች ወራሾች የሌሉ ከሆነ ግን ሥሙን ያለ ፈቃድ ለመጠቀም ይቻላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ግልፅ የሆነ ድንጋጌ አልተቀመጠም፡፡ በመሆኑም ድንጋጌው የሚያገለግለው በህይወት ለሚኖሩ ታዋቂ ሰዎች ስም ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

**የሚመዘገበው ስም በኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ሥምነት ያልተመዘገበ ቢሆንም በሌሎች አገራት የሚታወቅ ወይም ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ካላቸው ስሞች መካከል መሆን የለበትም**

ይህ ድንጋጌ የሚመለከተው ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተመዘገቡ የተወሰኑ የንግድ ስሞችን ነው፡፡ ሁለት ዓይነት ሥሞችን የሚመለከት ነው፡፡ አንደኛው በሌሎች አገራት የሚታወቅ ስም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያለው ሥም ነው፡፡



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

በሌሎች ሀገራት ልምድ እንደሚታየው በአንድ ሀገር ሕግ መሠረት ያልተመዘገበ የንግድ ሥም ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂነት ያላቸው የንግድ ሥሞች ጥበቃ የሚደረግላቸው በሀገሮች መካከል በሚደረግ ሥምምነት መሰረት ነው፡፡ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጁ ግን ስምምነት ቢኖርም ባይኖርም በሌሎች ሀገራት የሚታወቁና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸውን የንግድ ስሞች ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡

በሌሎች ሀገራት ታዋቂ የሆኑ ስሞች ይኖራሉ፡፡ ይሁንና እነዚህን ሥሞች ለማወቅ ቀላል ላይሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌም አንድ  የንግድ ስም በሩዋንዳ የታወቀ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህንን ስም ኢትዮጵያ ውስጥ ለማወቅ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ለዚህ ስም ኢትዮጵያ ውስጥ ጥበቃ የሚደረግበት ምክንያት ግልፅ አይደለም፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ ያልተመዘገበ ነገር ግን በሌሎች ሀገራት ታዋቂ የሆነ የንግድ ስም ጥበቃ የሚደረግለት በኢትዮጵያ የሚታወቅ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የማይታወቅ ከሆነ የማይመዘገብበት ምክንያት የለም፡፡ በኢትዮጵያ የሚታወቅ  ሲባል ግን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያውቀው ይገባል ማለት አይደለም፡፡ የንግድ ሥሙ በሚታወቅበት የንግድ ዓይነት ወይም ሴክተር ኢትዮጵያ ውስጥ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ አክሰስ ባንክ በናይጀሪያ የታወቀ ስም ሲሆን በኢትዮጵያ የባንክ ሴክተርም የታወቀ ስም በመሆኑ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ የሚሸፍን ይሆናል፡፡

በአለም ዓቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ የንግድ ስሞችም አሉ፡፡ ኮካ- ኮላ፣ አፕል፣ ሶኒ፣ ማይክሮ ሶፍት፣ ስታርባክስ፣ ሒልተን ፣ ቶዮታ ወዘተ በሰፊው ከሚታወቁ የንግድ ስሞች ጥቂቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ስሞች ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ስምነት ባይመዘገቡም በኢትዮጵያውያን ዘንድ በስፋት የሚታወቁ ስሞች ናቸው፡፡ እነዚህን ሥሞች ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ስምነት ማስመዝገብ የሚቻለው ስሙን ለማስመዝገብና ለመጠቀም ፈቃድ መሰጠቱን የሚያሳይ ማረጋገጫ ሲቀርብ ነው፡፡ የሚቀርበው ማረጋገጫ የተለየ ፎርማት ባይኖረውም በፅሁፍ መሆን ይኖርበታል፡፡

- የአመልካቹ መጠሪያ ስም ወካይ ሲሆን ወይም
- ከንግድ ማህበራት አባላት ስም የተውጣጣ ከሆነ የአባላቱን ስሞች የመጀመሪያ ፊደላት ብቻ የያዘ ሲሆን ነው፡፡



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

አንዳንድ ምህፃረ ቃላት ትርጉም ያላቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ ትርጉም የማይሰጡ ይሆናሉ፡፡ በአዋጁ መሰረት ለንግድ ስምነት የቀረቡት ምህፃረ ቃላት ትርጉም ያላቸው ከሆነ ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ፡-ጉ.ተ ኢንተርኔት ካፌ (ጉና ተራራ)

- አ.ም ሎጅ (አርባ ምንጭ)
- ኪ..ም የአሸከርካሪዎች ማሰልጠኛ (ኪዳነ ምህረት)
- መ.ፎ የመንዐር ስራ (መልቲ ፎካል)
- መ.ታ ኮንስልተንሲ (መልቲ - ታለንት)

በተመሳሳይ መልኩ ለንግድ ስምነት የቀረበው ምህፃረ ቃል የአመልካቹ ስም ወካይ ከሆነም ሊመዘገብ ይችላል፡፡

ለምሳሌ፡

- ሸምሱ ሁሴን የሚባል ነጋዴ ሸ.ሁ ፍራፍሬ ንግድ" የሚል የንግድ ስም ሊኖረው ይችላል፡፡
- ከበደ ማሞ ቶላ የሚባል ነጋዴ "ከ.ማ.ቶ የመኪና ኪራይ" የሚል የንግድ ስም ሊኖረው ይችላል፡፡

ከንግድ ማህበራት አባላት ሥም የተውጣጣ ከሆነ ደግሞ የአባላቱን ስሞች የመጀመሪያ ፊደላት ብቻ የያዘ ሲሆን ምህጻረ ቃሉ በንግድ ስምነት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

ለምሳሌ በላይ፣ ኪሮስ፣ ስንቅነሽ እና ሴንጮ የሚባሉ ሰዎች አንድ የንግድ ማህበር ቢያቋቁሙ በ.ክ..ስ.ሴ የሚል የንግድ ስም ሊያስመዘግቡ ይችላሉ፡፡

ይህንን ድንጋጌ በተመለከተ ሁለት ነገሮች ግልፅ ሊሆኑ ይገባል፡፡ አንደኛው ድንጋጌው የሚመለከተው ምህፃረ ቃል ብቻ በንግድ ሥምነት ሲቀርብ ነው፡፡ ምህጻረ ቃሉ ከሌላ ቃላት ጋር ተጨምሮ ለንግድ ስምነት ሊቀርብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ "ጉ.ማ.ኔ አዋሽ ቆዳ ስራ" የሚል የንግድ ስም ለምዝገባ ቢቀርብ ጉ.ማ.ኔ የሚለው ምህፃረ ቃል ትርጉም ቢኖረውም ባይኖረውም ወይም የባለቤቱን ስም ይወክል አይወክል ሊመዘገብ ይችላል፡፡



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry
Archives
መዝገብ ቤት

ሁለተኛው ጉዳይ ምህፃረ ቃሉ ቀደም ብሎ ከተመዘገበ ስም ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይና አሳሳች ከሆነ ወይም ለሞራል ተቃራኒ ከሆነ ወዘተ በተዘረዘሩ ሌሎች ድንጋጌዎች መሰረት ላይመዘገብ ይችላል። ለምሳሌ ባምላኩ፣ ለማ እና ጌታሁን የተባሉ ሰዎች የስሞቻቸውን የመጀመሪያ ፊደል በመውሰድ "ባ.ለ.ጌ" የሚል የንግድ ስም ማስመዝገብ ቢፈልጉ ሥሙ ከመልካም ጠባይ ወይም ሥነ - ምግባር ተቃራኒ ነው ተብሎ ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል።

**በአዋጁ አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ረ) የንግድ ስም ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን የለባቸውም**

ለምዝገባ የቀረበ የንግድ ስም በተለያዩ ምክንያቶች ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ - ምግባር ተቃራኒ ሊሆን ይችላል። አንድ ስም ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን አለመሆኑ እንደ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያዩ ይችላል። አንድ ማህበረሰብ ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሚላቸው በሌላ ማህበረሰብ በተመሳሳይ ላይታዩ ይችላሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን በተለያዩ ሁኔታዎች ሊመጣ ይችላል።

**ለምሳሌ፡**

- አንድን ሀይማኖት የሚያንቋሽሽ ሥም፣
- አንድን ቋንቋ ብሔር /ብሔረሰብ የሚያንቋሽሽ ስም፣
- ስካርን፣ ሴሰኝነትን፣ አደንዛዥ ዕፅን፣ ወንጀልን የሚያበረታታ ስም
- የአንድን ሰው መልካም ዝና የሚያጎድፍ ስም
- የአንድ ፆታ የበታችነት የሚያመለክት ስም፣
- ጦርነትን፣ ብጥብጥን የሚያበረታታ
- ጥላቻን የሚያመላክት
- የሀገሪትን መልካም ስም የሚጎዳ ስም ወዘተ...

አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 (ረ) አንድ ስም ለመልካም ጠባይ ወይም ሰነ- ምግባር ተቃራኒ መሆን አለመሆን በእያንዳንዱ ሁኔታ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። በአሁኑ ዘመን ግልፅ በሆነ መልኩ ለመልካም ጠባይ ወይም ለስነ-ምግባር ተቃራኒ የሆኑ የንግድ ስሞች በጣም ውስን ሊሆኑ ቢችሉም ሙሉ በሙሉ የሉም ማለት ግን አይቻልም። ይህ በሚያጋጥምበት ወቅት እንደ አጠቃቀሙ ሁኔታ (context) መወሰን ይኖርበታል።



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives

ለምሳሌ፡- "ፍለርት ባር" (Flirt Bar) የሚለው የንግድ ስም ለምዝገባ ቢቀርብ ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ-ምግባር ተቃራኒ መሆን አለመሆኑ አጠያያቂ ሊሆን ይችላል። የእንግሊዘኛው ቃል "Flirt" መቀራረብን፣ መፈላለግን፣ መነካካትን ወዘተ የሚያሳይ ነው። ቃሉን በቡና ቤት ደረጃ ስንመለከተው ፆታዊ መቀራረብ፣ መተሻሸት ወዘተ የሚደረግበት ቦታን ሊያመለክት በመቻሉ ለመልካም ጠባይ ወይም ስነ- ምግባር ተቃራኒ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

በመጨረሻም በአዋጁ አንቀጽ14 የንግድ ስምና የድርጅት ስም ዘርፍን ጠቅሶ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ሲሆን ጀነራል፣ ኢንተርንሽናል፣ ግሩፕ፣ ቢዝነስ ፣ ኢንዱስትሪ፣ ኢንቨስትሜንት፣ አገልግሎት ዘርፍን የማያመለክቱ እና ለሦስተኛ ወገን እንዲሁም ለህብረተሰቡ የሚያሳስት መረጃን ሊያስተላልፍ የሚችል የቃላት አጠቃቀም በመሆኑ የዚህ አይነት አሰያየም ለንግድ ስምና ለድርጅት ስም እንዲውል አይደረግም።

የንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

# አባሪ IV የድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መረጃ ማሰባሰቢያ ቼክሊስትና ቅፅ



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

7.3.የሚሸጣቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ሕጋዊ ደረሰኝ

ሀ) ይሰጣል                ለ) አይሰጥም

8. አጠቃላይ በሥራ ላይ የታዩ ጉዳዮች

____________________

____________________

____________________

____________________

9. የኢንስፔክተሩ አስተያየት

____________________

____________________

____________________

____________________

10. ኢንስፔክሽን የተካሄደበት ቀን ____________ ሰዓት ________

11. የኢንስፔክሽን ስራውን ያካሄደው ኢንስፔክተር ስምና ፊርማ

| ስም | ፊርማ |
|---|---|
| 1. ____________ | ________ |
| 2. ____________ | ________ |
| 3. ____________ | ________ |
| 4. ____________ | ________ |

12. ኢንስፔክሽን በተካሄደበት ወቅት የነበረው የንግድ ድርጅት ባለቤት/ኃላፊ/ተወካይ/ሠራተኛ

| ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| 1. ____________ | ________ | ________ |

ንግድ ሚኒስቴር Ministry of Trade Archives መዝገብ ቤት

| የኢፌዲሪ ንግድ ሚኒስቴር | |
|---|---|
| በውጭ ድህረ-ፈቃድ ኢንስፔክሽን ሥራ አማካኝነት ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የተለዩ ድርጅቶችን መረጃ መመዝገቢያ ቅጽ | የተሰጠው ቁ. |

| ተ.ቁ | የግብር መለያ ቁጥር | የንግዱ/የድርጅት ስም | ክልል | ከተማ | ክፍለ ከተማ | ወረዳ/ቀበሌ | የቤ.ቁጥር | የስልክ ቁጥር | የንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር | የንግድ ሥራው ዘርፍ | ፈቃዱ ለመጨረሻ ጊዜ የታደሰበት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |

ሥራው እንዲሠራ ያጸደቀው ቡድን መሪ ሥም ____________________

ፊርማ ____________________

ሥራውን የተረከበው መሪ ኢንስፔክተር ሥም ____________________

ፊርማ ____________________

ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት